# አዲስ ዘመን

ማክሰኞ | 83ኛ ዓመት ቁጥር 316 ሐምሌ 16 ቀን 2016 ዓ.ም ዋጋ 10.00 | ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!




## "የሠላም ካውንስሉን ጥሪ ተቀብለው ከሚመጡ ታጣቂዎች ጋር ችግሮችን በድርድር ለመፍታት ዝግጁ ነን"

*- መንገሻ ፈንታው (ዶ/ር)*
*የአማራ ክልል ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ*

**ማርቆስ በላይ**

አዲስ አበባ:- የክልሉ መንግሥት የሠላም ካውንስሉን ጥሪ ተቀብለው ከሚመጡ የታጠቁ ኃይሎች ጋር ችግሮችን በድርድር ለመፍታት ዝግጁ ነው ሲሉ የአማራ ክልል ኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ መንገሻ ፈንታው (ዶ/ር) ገለጹ።

የአማራ ክልል የኮሙኒኬሽን ቢሮ ኃላፊ መንገሻ ፈንታው (ዶ/ር) ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ የክልሉ መንግሥት የሠላም ካውንስሉን ጥሪ ተቀብለው ከሚመጡ የታጠቁ ኃይሎች ጋር ችግሮችን በድርድር ለመፍታት ዝግጁ ነው።

በክልሉ የሠላምና ፀጥታ ችግሮችን ተከትሎ የሕግና የፀጥታ ማስከበር ሥራ ሲሠራ ቆይቷል ያሉት ኃላፊው፤ የሠላም ሁኔታው ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ መጥቶ በርካታ አካባቢዎች ላይ ሕዝቡ የሠላም አየር እየተነፈሰ ይገኛል ብለዋል፡፡

አንጻራዊ ሠላሙን ዘላቂ ለማድረግ ከሕግ ማስከበር ጎን ለጎን መሣሪያ አንግበው የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች የሠላም ጥሪ እየተላለፈ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

የክልሉ መንግሥት በማንኛውም መንገድ ለሠላም ምን ጊዜም በሩ ክፍት መሆኑን የገለጹት

"የሠላም ካውንስሉን ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች
## በእኩልነት ላይ የተመሠረተ መዋቅራዊ ለውጥ ያስፈልጋቸዋል

**ሞገስ ፀጋዬ**

አዲስ አበባ:- ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች የተወሰኑ ሀገራትን የፖለቲካ ፍላጎት ከማሟላት ወጥተው በእኩልነት ላይ የተመሠረተ አገልግሎት እንዲሰጡ መዋቅራዊ ለውጥ እንደሚያስፈልጋቸው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ታዬ አፅቀሥላሴ አስታወቁ።

አራተኛው የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የዓለም አቀፉን የፋይናንስ ለልማት ጉባኤ ቅድመ ዝግጅት ስብሰባ ከትናንት ጀምሮ በአዲስ አበባ እየተካሄደ ነው።

በጉባኤው ላይ ንግግር ያደረጉት የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አምባሳደር ታዬ አፅቀሥላሴ እንደገለጹት፤ ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች ከተቋቋሙ ረጅም ጊዜን አሳልፈዋል። ነገር ግን የተወሰኑ ሀገራትን የፖለቲካ ፍላጎት የሚያሟሉ ሆነው ዘልቀዋል። እንደ አይ ኤም ኤፍና የዓለም ባንክ ያሉ ድርጅቶች ዘመኑን መምሰል አለባቸው። የታዳጊ ሀገሮችን ጥያቄ ማስተናገድ መቻል አለባቸው፤ ይህን ለማድረግ ደግሞ ሰፊ የሆነ መዋቅራዊ ለውጥ ያስፈልጋቸዋል። መዋቅራዊ ለውጡ አካታችና በእኩልነት ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት ነው ያሉት።

እ.ኤ.አ በ2015 በዘላቂ ልማት ዘሪያ የተቀመጡ ግቦችን ለማሳካት ዓለም አቀፍ መሪዎችና የፋይናንስ ባለሙያዎች ለመጀመሪያ ጊዜ እንዴት ፋይናንስ መደረግ እንዳለባቸው ሰፊ ውይይት ማድረጋቸውን አውስተው፤ በአስር ዓመቱን ጉዞ ውስጥ ሊደነቅ የሚችል ውጤት አልመጣም፤ ነገር ግን የተወሰነ ለውጥ መመዝገቡን ጠቅሰዋል።

የዘላቂ ልማት ግቦች ውጤታማ እንዲሆን ዓለም

ዓለም አቀፍ የገንዘብ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል





ፎቶ - ሃዲስ አብርሃ

አቶ አሕመድ ሺዴ

## ያደጉ ሀገራት በማደግ ላይ ያሉ ሀገራትን ታሳቢ ያደረገ የፋይናንስ ሥርዓት ሲዘረጉ ይገባል

**ቃልኪዳን አሳዬ**

አዲስ አበባ፡ ያደጉ ሀገራት በማደግ ላይ ያሉ ሀገራትን ታሳቢ ያደረገ ፍትሐዊ የፋይናንስ ሥርዓት ሊዘረጉ እንደሚገባ እየተካሄደ በሚገኘው አራተኛው የፋይናንስ ለልማት ቅድመ ጉባኤ ላይ ተገለጸ፡፡

ያደጉ ሀገራት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

## "ዘመናዊ የፖለቲካና የዲሞክራሲ ሥርዓት ለመገንባት የሚያስችል ምክክር አድርገናል"

*- አቶ ደስታ ዲንቃ*
*የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሰብሳቢ*

**ሳሙኤል ወንደሰን**

አዲስ አበባ:- የፖለቲካ ፓርቲዎች ዘመናዊ የፖለቲካና የዲሞክራሲ ሥርዓት ለመገንባት የሚያስችል ምክክር ከኢፌዲሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጋር አድርገናል ሲሉ የኢትዮጵያ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት ሰብሳቢ አቶ ደስታ ዲንቃ ገለጹ።

የኢትዮጵያ ፖለቲካ ፓርቲዎች ተወካዮች በሀገራዊ ስትራቴጂያዊ ጉዳዮች ላይ ከኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጋር ትናንት ውይይት አካሂደዋል።

የጋራ ምክር ቤቱ ሰብሳቢ አቶ ደስታ ዲንቃ ስለውይይቱ ለኢፕድ እንደገለጹት፤ ውይይቱ በተፎካካሪ ፓርቲዎችና በገዢ ፓርቲ መካከል የሚፈጠሩ አለመግባባቶችን በውይይትና በንግግር ለመፍታት ያለመ ነው። ይህም በገዢው ፓርቲ እና በተፎካካሪ ፓርቲዎች መካከል ያለውን ተግባቦት ለማጠናከር ጉልህ ሚና አለው።

ለሀገርና ለትውልድ የሚያስቡ ፖለቲከኞች ሰከን ብለው ሀገሪቱ ያለፈችበትን የፖለቲካ ጉዞዎች ለመቀየር



እና የተሻለ የፖለቲካ ሥርዓት ለመገንባት የተሰባሰቡበት የውይይት መድረክ ነው ያሉት አቶ ደስታ፤ በዚህም ከኢፌዴሪ ጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ጋር ዘመናዊ የፖለቲካና የዲሞክራሲ ሥርዓት ለመገንባት የሚያስችል ምክክር አድርገናል ብለዋል።

"ዘመናዊ የፖለቲካና ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል




# ለብዙዎች ተስፋ የሰነቀው - "በፍራ እናት"

ፋንታነሽ ክንዴ

**ዜና ሐተታ**

በማዕከላዊ ኢትዮጵያ ክልል ቡታጅራ ከተማ ጎራ ብለናል። ከአውራ ጎዳናው ጥቂት ገባ እንዳልን የእናት ጓዳን የሚያስታውስ ድንቅ መዓዛ ተቀበለን። መልካም መዓዛውን እያጣጣምን ወደ ውስጥ ዘለቅን። በዛም ቆሎ የሚያዘጋጁ፣ ለቆሎው ተጨማሪ ጣዕም የሚሰጡ ቅመማዎችን የሚያሰናዱ እንዲሁም ቆሎውን ለከተው የሚያሽጉ ብርቱ ሴቶችን አገኘን። እንደ ባሕላችን ሰላምታ አቅርበን ስንቀላቀላቸው በመዓዛው ከሩቅ የጠራንን ቆሎ በግብዣ አቀረቡልን። ጥሬውን እየቆረጠምን ስለ ሥራቸውና ተቋማቸው ያወጉን ዘንድ ጠይቀን ውይይታችን ቀጠልን።



በሦስት ብርቱ ወጣት ሥራ ፈጣሪዎች ተመስርቶ ዛሬ ላይ ለ270 ሴቶችና ለ50 ወንዶች የሥራ ዕድል የፈጠረው ኢንተርፕራይዝ "በፍራ እናት ባልትና" ይሰኛል። በኢንተርፕራይዙ ልብስና ጉርሳቸውን ከማሟላት አልፈው የሙያ ባለቤት በመሆን ነጋቸውን በትልቁ የሚያልሙ ጠንካራ ሠራተኞች አሉ።

በቀን እስከ 35 ኩንታል ቆሎ አምርቶ ለገበያ በሚቀርብበት ኢንተርፕራይዝ በርካታ ወጣቶች ጊዜያቸውን በሥራ ያሳልፋሉ። ሥራ ፈጣሪዎቹ ምርቱን ለማሳደግና ከሀገር ቤት አልፎ ወደአጎራባች ሀገራት ገበያ ለመግባት ያልማሉ።

የምሥራች ሳሙኤል በኢንተርፕራይዙ ምርት በማሸግ ሥራ ላይ ተሰማርታለች። ትምህርቷን አጠናቃ ቤት ቁጭ ለማለት ተገዳ ነበር። ይሁን እንጂ ወደዚህ ኢንተርፕራይዝ ከገባች በኋላ በሕይወቷ ላይ ብዙ ለውጥ መምጣቱን ትናገራለች። ዛሬ ላይ ከሚከፈለኝ ደመወዝ ባለፈ የትልቅ ሙያ ባለቤት መሆን ችያለሁ ትላለች።

የምሥራች እንደምትገልጸው፤ ድርጅቱ ከተጀመረ ገና አራት ዓመቱ ቢሆንም ለብዙዎችም ሥራ ዕድል ፈጥሯል። የምርቱ ተፈላጊነትም ከጊዜ ወደጊዜ እየጨመረ የሚመረተው ቆሎም እያደገ መጥቷል።

ኢንተርፕራይዙን ካቋቋሙ ወጣቶች ከራስ አልፎ ለሌሎች መትረፍን ተምሬያለሁ። እዚህ ተቀጥሬ ያገኘሁትን ሙያ ተጠቅሜ የራሴን ሥራ መፍጠርምና ለሌሎችም ተስፋ መሆን የነገ ሕልሜ ነው ትላለች።

ሴቶች አካባቢያቸው ላይ ያለውን ዕድል ሳይንቁ መሥራትና ሠርተው ራሳቸውን የሚችሉበትን ዕድል መፍጠር ይኖርባቸዋል የሚለው ደግሞ መልዕክቷ ነው።

ማርታ ሳሙኤል በበኩሏ፤ ሥራ የጀመረችው በ2015 ዓ.ም ነው። በ12ኛ ክፍል ብሔራዊ ፈተና የዩኒቨርሲቲ መግቢያ ውጤት ሳይመጣላት ሥራም ሳታገኝ የቤተሰብ ጥገኛ ሆና ነበር። አሁን ላይ በዚህ ሥራ ሕይወቷን መምራት የምትችልበት ሁኔታ ተፈጥሯል። በዚህ ነገን በበለጠ ተስፋ ትጠብቀዋለች።

ሥራ መግባቴ ትልቅ ለውጥ አግኝቼበታለሁ። ሥራ ቦታው መብትና ግዴታችንን ጠብቀን ነው። ሥራው ሲሠራ ምንም አይነት ንክኪ ሳይኖር በማሽን የሚከናወን በመሆኑ ሥራችንን አቅልሎልናል ትላለች።

ሥራ የለንም በሚል ጊዜያቸውን አልባሌ ቦታ የሚያሳልፉ ወጣቶች መኖራቸውን ጠቅሳ፤ ማንም ሰው በአካባቢው ያለውን ዕድል ተጠቅሞ ራሱን ለመለወጥ መትጋት እንዳለበትም ትገልጻለች።

ወደኢንተርፕራይዙ በ2015 ዓ.ም እንደገባች የምትናገረው ደግነሽ ዳዊት በበኩሏ ሥራው የእርሷ ጨምሮ የብዙዎችን ተስፋ እንዳለመለመ ነው የምታስረዳው።

ከአሻጊነት ጀምሮ በተለያዩ ክፍሎች በባለሙያነትና በአስተባባሪነት መሥራቷን ጠቅሳ፤ ወደዚህ ሥራ በመግባቷ የብዙ ሙያዎች ባለቤት ሆናለች። ድርጅቱ ደመወዝ ከመክፈል ባለፈ እንደ አስፈላጊነቱ የምግብ አቅርቦትና ሌሎችንም ጥቅማጥቅሞች ያቀርባል።

የኢንተርፕራይዙ መከፈት ቤት ቁጭ ብለው የሌሎችን እገዛ ይጠብቁ ለነበሩ እናቶችና ወጣቶች የሥራ ዕድል መፍጠሩን ጠቁማ፤ ሠራተኞችም በማኅበር ተደራጅተው እንደደመወዝ መጠናቸው በመቆጠብ ነገ ላይ የእኔ የሚሉት ሀብት እንዲኖራቸው ለማስቻል እየሠሩ ነው ትላለች።

ወጣቶች አቅሙ ካላቸው ሥራ መፍጠር ካልሆነም፤ የሚያገኙትን ዕድል ሁሉ አሟጠው በመጠቀም ነጋቸውን ብሩህ ማድረግ እንዳለባቸውም ነው መልዕክት ያስተላለፈችው።

# የአረንጓዴ ዐሻራ የዜጎችን የምግብ ዋስትና በማረጋገጥ ጉልህ ሚና እየተጫወተ ነው

ታደሠ ብናልፈው


ሱሉልታ፡- የአረንጓዴ ዐሻራ የዜጎችን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት ጉልህ ሚና እየተጫወተ መሆኑን የአፍሪካ አመራር የልህቀት አካዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት ወንድዬ ለገሠ (ዶ/ር) ተናገሩ።

የአፍሪካ የአመራር ልህቀት አካዳሚ አመራሮች፣ ሠራተኞች እንዲሁም በሸገር ከተማ የመና አቢቹ ክፍለ ከተማ አመራሮችና ማኅበረሰቡ በተቋሙ ቅጥር ግቢ ውስጥ ትናንት የችግኝ ተከላ መርሐ ግብር አካሂደዋል።

መርሐ ግብሩ ላይ ንግግር ያደረጉት የአፍሪካ የአመራር ልህቀት አካዳሚ ምክትል ፕሬዚዳንት ወንድዬ ለገሰ (ዶ/ር)፤ በኢትዮጵያ የአረንጓዴ ኢኮኖሚን በማሳደግ የዜጎችን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ በትኩረት እየተሠራ ነው። ይህም የዜጎችን የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ በሚደረገው ጥረት ጉልህ ሚና እየተጫወተ ይገኛል።

ኢትዮጵያ በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር አረንጓዴ ኢኮኖሚን እየገነባች ነው ያሉት ወንድዬ (ዶ/ር)፤ በተለይ ለምግብ የሚያገለግሉ ፍራፍሬዎችን መጠንና ምርት በማሳደግ ብልፅግናን እውን የማድረግ ሥራ እየተሠራ ነው ብለዋል።

አረንጓዴ ዐሻራ የአፈር መሸርሸርንና የአየር ንብረት ለውጥን በመከላከል ምርትና ምታማነትን በማሳደግ ረገድ ከፍተኛ ሚና እንዳለው ገልጸው፤ የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ ለተለያዩ የአፍሪካና የሀገር ውስጥ አመራሮችን አሠልጥኖ ብቁ ከማድረግ ባለፈ በቅጥረ ግቢው በሚገኝ 50 ሄክታር መሬት ላይ የተለያዩ የአረንጓዴ ልማቶችንና የአፈር ጥበቃ ሥራዎችን በማከናወን በስፋት እየተሳተፈ ነው ሲሉ



ወንድዬ ለገሰ(ዶ/ር)



አቶ አዲሱ ከተማ

አብራርተዋል።

በ2016 በጀት ዓመት አራት ሄክታር መሬት ላይ የነበረን የባሕር ዛፍ ደን በማስወገድ መሬቱን የማከምና እርከን የመሥራት ሥራዎች መከናወናቸውን አመልክተው፤ የታከመውንና እርከን የተሠራበትን መሬት በፍራፍሬ ተክሎች ለመሸፍን እየተሠራ መሆኑን ምክትል ፕሬዚዳንቱ ተናግረዋል።

በአንድ ቀንም ሦስት ሺህ የአፕል ችግኖችና ሌሎች ፍራፍሬዎች በአጠቃላይ አራት ሺህ 500 ችግኖችን የመትከል ሥራ ተከናውኗል ሲሉ ተናግረዋል።

በተቋሙ ግቢ ውስጥ የሚገኘውን 50 ሄክታር መሬት በምግብና በሀገር በቀል ችግኞች ለመሸፈን እየተሠራ ያለው ሥራ ትልቅ ኢንቨስትመንት የሚጠይቅ እንደሆነ ጠቁመው፤ ትልቅ መዋለ ንዋይ ፈሰስ አድርጎ ለማልማት እየተሠራ ነው ብለዋል።

50 ሄክታሩ መሬት ፍራፍሬና በአረንጓዴ ዐሻራ የማልማት ሥራ ሲጠናቀቅ፣ የአካባቢው ማኅበረሰብ በተመጣጣኝ ዋጋ ምርት ያገኛል፤ የተቋሙ የውስጥ ገቢ ያድጋል፤ ለሥልጠና ለሚመጡ ሠልጣኞችም እንደመናፈሻነትም ያገለግላል ሲሉ አብራርተዋል።

ተቋሙ የሚሰጣቸው ሥልጠናዎች ለአካባቢውን ማኅበረሰብ የሥራ ዕድል እንዲፈጠርለት፣ መሠረተ ልማት እንዲገነባለት እያደረጉ መሆኑን ገልጸው፤ ይህም ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ አመላክተዋል።

የመና አቢቹ ክፍለ ከተማ ግብርና ጽሕፈት ቤት ኃላፊ አቶ አዲሱ ከተማ በበኩላቸው፤ ተቋሙ በአረንጓዴ ዐሻራና በሥራ ዕድል ፈጠራ የአካባቢውን ማኅበረሰብ ተጠቃሚ እያደረገ ነው።

በዘንድሮው የአረንጓዴ አሻራ መርሐ ግብር ከ200 ሺህ በላይ ችግኝ በክፍለ ከተማውን ለመትከል በትኩረት እየተሠራ ነው ብለዋል።

ማኅበረሰቡን በአረንጓዴ ዐሻራ የምግብ ዋስትናውን ለማረጋገጥ እየተሠራ ነው፤ እየተሠራ ያለውም ሥራ ተጠናክሮ ይቀጥላል ሲሉ አመላክተዋል።

# ጎርፍ በሰብሎች ላይ ጉዳት እንዳያደርስ ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ ኢንስቲትዩቱ አሳሰበ

ሳሙኤል ወንደሰን

አዲስ አበባ፡- በመጪዎቹ አሥር ቀናት ጎርፍ በሰብሎች፣ በእንስሳትና በንብረት ላይ ጉዳት እንዳያደርስ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ የኢትዮጵያ ሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት አስታወቀ።

ኢንስቲትዩቱ ለኢፕድ በላከው መግለጫ እንደገለጸው፤ በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በአንዳንድ አካባቢዎች ላይ ከሚጠበቀው ከባድ ዝናብ ጋር ተያይዞ ቅጽበታዊ ጎርፍ እና የመሬት መንሸራተት ሊከሰት ይችላል። በተለይም በተከታታይ ዝናብ እያገኙ ባሉ እና ከባድ ዝናብ በሚጠበቅባቸው ቦታዎች አርሶ አደሩ እና የሚመለከታቸው አካላት በጋራ በመሆን በሰብሎች፣ በእንስሳትና በንብረት ላይ ጉዳት እንዳይደርስ ተገቢውን ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

ኢንስቲትዩቱ እርጥበቱ ከመጠን በላይ ሊሆን ስለሚችል በዚህም ምክንያት ውሃ ማሳ ላይ እንዳይተኛ ቦይ በማውጣት የማንጣፈፍና የመከላከል ሥራ መሥራት እንደሚገባ አሳስቧል።

አረምን በወቅቱ በማረም፣ ፀረ-አረምና ፀረ-ተባይ ኬሚካሎችን አጠቃቀም ረገድ በወቅቱ ከግብርና ባለሙያ በሚያገኙት ምክረ ሀሳብ መሠረት የዝናቡን ሁኔታ ባገናዘበ መልኩ ማከናወን እንደሚያስፈልግ ገልጿል።

በሚቀጥሉት ቀናት የመኸር አምራችና የክረምት ተጠቃሚ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተስፋፋ የእርጥበት ሁኔታ እንደሚኖራቸው ይጠበቃል። ይህም ሁኔታ ለግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ የጎላ ጠቀሜታ እንደሚኖረው በመግለጫው አመላክቷል።

ከዚህም ጋር ተያይዞ አስቀድመው ተዘርተው በተለያየ የእድገት ደረጃ ላይ ለሚገኙ የመኸር ሰብሎች በጎ ሚና ይኖረዋል ያለው መግለጫው፤ የመኸር ወቅት እርሻ እንቅስቃሴን ዘግይተው ለሚጀምሩ አካባቢዎች የአፈር ውስጥ እርጥበትን እንደሚያሻሽልና የመኸር ሰብሎችን በወቅቱ ለመዝራት ምቹ ሁኔታን እንደሚፈጥር ይጠበቃል ተብሏል።

በተጨማሪም ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላት እና በአሁኑ ጊዜ እርጥበት በማግኘት ላይ ለሚገኙት በምሥራቅ እና በሰሜን ምሥራቅ ለሚገኙት አርብቶ አደሮችና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽና የመጠጥ ውሃ አቅርቦት መሻሻል የጎላ ጠቀሜታ እንደሚኖረው ተገልጿል።

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት በአብዛኛው ዓባይ፣ ተከዜ፣ አዋሽ፣ ባሮአኮቦ፣ የላይኛው እና የመካከለኛው ኦሞጊቤ፡ አፋር ደናክል፤ ስምጥ ሸለቆ፣ ዋቤ ሸበሌ እና የገናሌ ዳዋ ተፋሰሶች ላይ ከመጠነኛ እስከ ከፍተኛ የእርጥበት ሁኔታ ይኖራቸዋል ብሏል።

ይህም የእርጥበት ሁኔታ የገጸ ምድር እና የከርሰ ምድር ውኃን ከማሻሻል እንዲሁም የግድቦችን እና የወንዞች የውኃ አቅም ከማጎልበት አንጻር ጥሩ አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል።

በሌላ በኩል በአንዳንድ ተፋሰሶች ላይ ሊኖር ከሚችለው ከፍተኛ የእርጥበት ሁኔታ ጋር ተያይዞ ቅጽበታዊ ጎርፍ እንዲሁም የወንዝ ዳርቻዎች ውሃ ሙላት ክስተቶች በተለይም ለጎርፍ ተጋላጭ በሆኑና በከተሞች አካባቢዎች ላይ ተፅዕኖ እንዳያጋጥም ከወዲሁ አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረግ እንደሚያስፈልግ በመግለጫው አስታውቋል።


ዜና

# “የኮሪደር ልማቱ ለዜጎች ምቹ ከተማ በመገንባት ሂደት ምሳሌ መሆን ይችላል”

- ዳንኤል ሊሬቦ (ዶ/ር)

በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የከተማ ዲዛይንና ፕላን ምሑር

**በኃይሉ አበራ**



አዲስ አበባ፦ በአዲስ አበባ እየተከናወነ የሚገኘው የኮሪደር ልማት ለዜጎች ምቹ የሆነ ከተማን በመገንባት ሂደት ምሳሌ መሆን የሚችል ሥራ ነው ሲሉ በኢትዮጵያ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የከተማ ዲዛይንና ፕላን ምሑሩ ዳንኤል ሊሬቦ (ዶ/ር) አስታወቁ።

በአዲስ አበባ እየተካሄደ ባለው የኮሪደር ልማት ላይ ሃሳባቸውን ለኢፕድ ያጋሩት ዳንኤል ሊሬቦ (ዶ/ር)፤ አዲስ አበባ ከነበረችበት ውስብስብ ችግሮች ተላቃ ደረጃዋን በሚመጥን መልኩ ዳግም እየለማች ነው ብለዋል።

ተገቢ የሆኑ የተሽከርካሪ መንገዶች፣ የእግረኛ መሄጃዎች፣ የፍሳሽና የቆሻሻ ፍሳሽ ማስወገጃ ቱቦዎች፣ የንፁሕ መጠጥ ውሃ መስመር፣ የመብራትና የቴሌ መስመሮች በሙሉ በተናበበ መልኩ እየተሠሩ መሆናቸውን የኮሪደር ልማቱ ውጤታማ መሆኑን ያሳያል ሲሉ ተናግረዋል።

የኮሪደር ልማቱ ዘላቂ የሆነ የተቀናጀ የመሠረተ ልማት ፕላን እንዲዘጋጅ አድርጓል ያሉት ምሑሩ፤ ኮሪደሩ በግራና ቀኝ የኪነ ሕንፃ ጥበባቸውን የተጠበቁ ፣ ለዓይን ማራኪ የሆኑና ቦታዎችን መናፈሻዎች እንዲገነቡ አስችሏል ሲሉ አስረድተዋል።

ልማት የከተማ ዲዛይን አንዱ ሞዴል ነው፤ ሌሎች ሀገራትም ይሄንን ተግባራዊ አድርገዋል። በቀጣይም ከአዲስ አበባ ውጪ ያሉ የኢትዮጵያ ከተሞች ሊከተሉት የሚገባ ልማት ነው ብለዋል።

የኮሪደር ልማቱ በመዲናዋ ሰው በነፃነት የሚንቀሳቀስበት፣ የሚኖርበት፣ የሚዝናናበት ቦታ ከመፍጠሩ በላይ የቱሪዝም መስሕብና የውበት ከተማ እንድትሆን እንዲሁም ዘላቂ ልማትን ለማረጋገጥ የመጣ አሠራር መሆኑን አስታውቀዋል።

ከተማዋ አሁን ይበል በሚያሰኝ ደረጃ ላይ ትገኛለች ያሉት ዳንኤል (ዶ/ር)፤ ሥራውን በማጠናከር ለሚቀጥለው ትውልድ ጭምር መዲናዋ የመኖሪያ፣ የንግድ፣ የማምረቻ፣ የሥራ ፈጠራ፣ የቱሪዝም ማዕከል እንድትሆን ማድረግ ተገቢ መሆኑን አመላክተዋል።

አዲስ አበባ የአፍሪካ ኅብረት ዋና ከተማ፣ የተባበሩት መንግሥታት የኢኮኖሚክ ኮሚሽን ዋና ከተማ መሆኗ ከሌሎች ከተሞች ልዩ ባሕሪ እንዲኖራት ማድረጉን ገልጸዋል።

በዓለም ካሉት የዲፕሎማቲክ ከተሞች አንዷ ናት መሆናን ጠቁመው፤ መዲናዋ ያላትን ፀጋ ሳትጠቀም መቆየቷን አንስተዋል። ችግሩን ግምት ውስጥ በማስገባት አዲስ አበባ ዳግም እየለማችና የዲፕሎማሲ ማዕከልነቷን የሚያጠናክር ደረጃ እንድትይዝ የኮሪደር ልማቱ ወሳኝ መሆኑን ተናግረዋል።

ቀደም ሲል የመብራት፣ የፍሳሽ ማስወገጃ፣ የቆሻሻ አወጋገድ ሥርዓት ጨምሮ ሰፋፊ ችግሮች እንደነበሩ ጠቁመው፤ በኮሪደር ልማቱ አሁን በግልጽ የታየውን ለውጥ እያመጣ ይገኛል ብለዋል።

የእግረኛ መሄጃ ክፍት ስፍራዎች፣ የብስክሌት መሄጃዎች፣ በየቦታው ባሉ ኪስ ቦታዎች ዛፎችን በመትከልና አረንጓዴን ስፍራዎችን የመፍጠር ሥራዎች እየተሠሩ መሆኑን በበጎነት አንስተዋል።

አሁን መዲናዋ ሌሎችም ጥሩ ምሳሌ በምትሆንበት ደረጃ ላይ እንደምትገኝ አመላክተው፤ በኮሪደር ልማቱ አማካኝነት ከተሞች እንዴት ውበታቸውን አጉልተው ማሳየት እንደሚችሉ ማሳየት ተችሏል ሲሉ ተናግረዋል።

በኮሪደር ልማቱ የሚታዩት ተስፋ ሰጪ እንቅስቃሴዎች በክልል ከተሞችም መጀመሩን ጠቅሰው፣ ይህም ተጠናክሮ መቀጠል እንዳለበት አመላክተዋል።

ሌሎች ከተሞችም የቱሪዝም፣ የንግድ፣ የማምረቻ፣ የመናፈሻ ማዕከላት እንዲሆኑ የየራሳቸውን ልማት በማከናወን ሚናቸውን ሊወጡ እንደሚገባም ጠቁመዋል።

# የኅብረት ሥራ ማኅበራቱ የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋት የበኩላቸውን ሚና እየተወጡ ነው

**አማን ረሺድ**

አዲስ አበባ፦ የኅብረት ሥራ ማኅበራት የተለያዩ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ ለሸማቹ በማቅረብ የኑሮ ውድነትን ለማረጋጋት የበኩላቸውን ሚና እየተወጡ መሆኑን የሲዳማ ክልል ኅብረት ሥራ ኤጀንሲ አስታወቀ።

የኤጀንሲው ኃላፊ አቶ ሽመልስ ሀጢሶ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በክልሉ የሚገኙ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ለሸማቹ ምርቶችን በተመጣጣኝ ዋጋ በማቅረብ የምርት አቅርቦት እጥረት እንዳይከሰትና የዋጋ ንረት እንዳይፈጠር ሰፊ ሥራ እያከናወኑ ነው።

አቶ ሽመልስ እንዳመላከቱት፤ በክልሉ መሠረታዊ የሸማች ማኅበራትን ጨምሮ በተለያዩ ዘርፎች ከሁለት ሺህ 500 በላይ የኅብረት ሥራ ማኅበራት ይገኛሉ። ማኅበራቱ ከሦስት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር በላይ በማንቀሳቀስ በኢኮኖሚው ውስጥ ትልቅ አቅም ገንብተዋል።

ማኅበራቱ አምስት መቶ ሺህ አባላት እንዳላቸው የገለጹት ኃላፊው፤ ለኅብረተሰቡ የግብርና ውጤቶችን ጨምሮ የተለያዩ ምርቶችን ተደራሽ በማድረግ የኑሮውን ጫና እያቃለሉ ነው ብለዋል።

የሸማች ኅብረት ሥራ ማኅበራቱ ከአርሶ አደሩ ጋር ትስስር በመፍጠር ምርቶችን በቀጥታ ወደ ገበያ በማቅረብ የተረጋጋ ግብይት እንዲኖር በማድረግ በኩል ትልቅ አስተዋፅዖ ማበርከታቸውን ገልጸዋል።

ኤጀንሲው ማኅበራቱ ለኅብረተሰቡ የሚሰጡትን አገልግሎት ወደ ላቀ ደረጃ ለማሳደግ የሪፎርም ሥራ ከዞን አስከ ወረዳ ድረስ እየሠራ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

የኅብረት ሥራ ማኅበራቱ የምርት አቅርቦት ችግሮች እየተስተዋለባቸው መሆኑን አመላክተው፤ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በቅንጅት እየተሠራ እንደሚገኝ አስረድተዋል።



በክልሉ የሚገኙ 377 የሸማች ማኅበራት የገበያ ማረጋጋት ሥራ ሠርተዋል

በክልሉ አቮካዶ፣ አናናስ፣ ማርና ቅቤ በብዛት የሚገኝ በመሆኑ ማኅበራቱ ከክልሉ አልፈው አዲስ አበባ በተገነቡ የገበያ ማዕከላት የተለያዩ ምርቶችን እያቀረቡ እንደሚገኙ አመላክተዋል።

በክልል ደረጃ 377 የሸማች ማኅበራት የገበያ ማረጋጋት ሥራ ሲሠሩ መቆየታቸውን ጠቅሰው፤ ኤጀንሲው ከአጎራባች ክልሎች ጋር የገበያ ትስስር በመፍጠር የግብይት ሥርዓቱ ጤናማ እንዲሆንና ምርቶች በሚፈለገው መጠን ለተጠቃሚው እንዲቀርቡ በትኩረት እየሠራ ይገኛል ብለዋል።

በተጨማሪም ማኅበራቱ የቁጠባ ባሕል እንዲዳብር በማድረግ ለማኅበሩ አባላትና ለሌሎች ዜጎች የሥራ ዕድል በመፍጠር የራሳቸውን ድርሻ እየተወጡ ይገኛል ሲሉ አንስተዋል።

ዜጎችን ከድህነት ለማላቀቅ የሚደረገውን ትግል ውጤታማ ለማድረግ ኅብረት ሥራ ማኅበራት ሊጠናከሩ እንደሚገባ ተናግረዋል።

የኅብረት ሥራ ማኅበራት በሚፈለገው መጠን ምርት እንዳያቀርቡ የምርትና የገንዘብ እጥረት ማነቆ ሆኗል ያሉት ኃላፊው፤ የኅብረተሰቡን የኑሮ ጫና ከማቃለል አኳያ ኤጀንሲው ችግሩን ለመቅረፍ የተለያዩ እገዛዎችን ከማድረግ ባለፈ ከመንግሥት ጋር በመቀናጀት ችግሮቹን እየፈታ መሆኑን ገልጸዋል።

# የመድኃኒት ደኅንነት ቁጥጥርን ለማጎልበት ኅብረተሰቡም ሆነ የጤና ባለሙያዎች ኃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል

**ታምራት ተስፋዬ**

አዲስ አበባ ፦ የመድኃኒት ደኅንነት፣ ፈዋሽነትና ጥራት ቁጥጥርን ለማኅልበት ኅብረተሰቡም ሆነ የጤና ባለሙያዎች የበኩላቸውን ኃላፊነት መወጣት እንዳለባቸው የኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን አሳሰበ።

የባለሥልጣኑ የመድኃኒት ደኅንነት ክትትልና የሕክምና ሙከራ መሪ ሥራ አስፈፃሚ አስናቀች ዓለሙ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለፁት፤ የመድኃኒት ደኅንነት ቁጥጥር በገበያ ላይ ስላሉ መድኃኒቶች ደኅንነት መረጃ የሚሰበሰብበት፣ የሚተነተንበትና እንደ አስፈላጊነቱ ለማስተማሪያነትና ችግሮችን ለመከላከል የሚያስችል ሥርዓት ነው።

የመድኃኒቶችን ደኅንነት፣ ፈዋሽነትና ጥራት ቁጥጥርን ለማኅልበት ኅብረተሰቡም ሆነ የጤና ባለሙያዎችና ባለድርሻ አካላት የበኩላቸውን ኃላፊነት መወጣት እንዳለባቸው መሪ ሥራ አስፈፃሚዋ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

"ሁሉም ሰው በመድኃኒቶች ደኅንነት ጉዳይ ይመለከተዋል፤ ከመድኃኒት ደኅንነት ጋር የተያያዘ ክስተት ሲያጋጥም ለኢትዮጵያ የምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን ወይም ለክትትል ማዕከላትና በነፃ የስልክ መስመር 8482 በፍጥነት ሪፖርት ማድረግ ይገባዋል” ብለዋል።

መድኃኒቶች ተጠንተው ጥቅም ላይ ሲውሉና የገበያ ፈቃድ በሚያገኙበት ወቅት ስለ መድኃኒቱ የሚኖሩ የደኅንነት መረጃዎች ውስን በመሆናቸውና መድኃኒቶች በስፋት ጥቅም ላይ በሚውሉበት ወቅት ቀጣይነት ያለው ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል ሲሉ አስረድተዋል።

የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ባለሥልጣን በአዋጅ በተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት መሠረት ገበያ ላይ የሚውሉ መድኃኒቶችን ደኅንነት፣ ፈዋሽነትና ጥራት ለማረጋገጥ የተለያዩ የአሠራር ሥርዓቶችን መዘርጋቱን ጠቁመዋል።

የመድኃኒት ደኅንነት ቁጥጥርን ለማረጋገጥ በተለይ ባለፉት ሁለት ዓመታት የተለያዩ የመድኃኒት የጎንዮሽ ክስተት ሪፖርት ማድረጊያ ቅጾችን በማዘጋጀትና በማሰራጨት፣ የግንዛቤና አቅም ማጎልበቻ ሥልጠናዎችን በመስጠት፣ የአሠራር መመሪያዎችን በማዘጋጀት ውጤታማ ተፈፃሚነታቸው ላይ ክትትል እየተደረገ ይገኛል ብለዋል።

በአቅም ግንባታ ረገድ ከስምንት ሺህ በላይ ለሆኑ ባለሙያዎች ሥልጠና መሰጠቱንና በተለያዩ አካባቢ በሚገኙ ሰባት የዩኒቨርሲቲ ሆስፒታሎች ስድስት የክትትል ማዕከላት ማደራጀቱን የጠቆሙት ወይዘሮ አስናቀች፤ በቁጥጥር ሥራው ወደ ዓለም አቀፉ የመረጃ ቋት የሚላኩ ሪፖርቶችን በመጨመርና በሀገር አቀፍ ደረጃ ከፍተኛ ለውጥ ማስመዝገብ መቻሉን አንስተዋል።

የጤና ባለሙያዎች የመድኃኒት አወሳሰድ ሥርዓትና ከመድኃኒት ጋር ተያይዘው ስለሚያጋጥሙ የጎንዮሽ ክስተቶች ለታካሚዎች ቀድመው የማሳወቅና ችግሮች ሲከሰቱም አስፈላጊውን ሕክምና የመስጠት ኃላፊነት እንዳለባቸው አመላክተው፣ ከዚህ ባሻገር የጎንዮሽ ክስተቶችንም ወደ ምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን ሪፖርት ማድረግ እንዳለባቸው አስታውቀዋል።

በየደረጃው የሚገኙ የተቆጣጣሪ አካላት ስለመድኃኒት የጎንዮሽ ክስተት የማሳወቅ፣ የጤና ባለሙያውን ስለ መድኃኒት የጎንዮሽ ክስተቶች ላይ ማሠልጠንና የክትትል ሥርዓቱን ለማከናወን የሚያስፈልጉ ግብዓቶችን ማለትም፡ መመሪያ፣ ጋይድላይን፣ ሪፖርት ማድረጊያ ቅጾችን ለጤና ተቋማት የማዳረስ እና የጎንዮሽ ክስተቶች ሪፖርቶችን የመሰብሰብ ኃላፊነት አለባቸው ብለዋል።

የመድኃኒቶችን ደኅንነት፣ ፈዋሽነትና ጥራት ቁጥጥርን ለማኅልበት በሚከናወኑ ተግባራት የሰዎችን ጤና ከማስጠበቅና ከአደጋ ከመከላከል ባሻገር እንደ ሀገር የጤናው ዘርፍ የሚኖረው ፋይዳም ከፍተኛ መሆኑን አመላክተዋል።

የኢትዮጵያ ምግብና መድኃኒት ቁጥጥር ባለሥልጣን በልዩ ትኩረት የመድኃኒቶች ደኅንነት ክትትል ሥርዓቱን ለማጠናከር ፣ የሕግ ማዕቀፎችን በማሻሻል፣ የባለሙያዎች አቅም ግንባታና ክትትልን በማጠናከር፣ የመድኃኒቶች ደኅንነትን አስመልክቶ በሚነሱ ጉዳዮች አስፈላጊና ወቅታዊ ርምጃ በመውሰድ፣ ኅብረተሰቡን የቁጥጥሩ ባለቤት እንዲሆን ማድረግን ጨምሮ የግንዛቤ ማዳበር ሥራዎችን ይበልጥ እየሠራ መሆኑን አብራርተዋል።

ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ. በ2009 የዓለም ጤና ድርጅት የዓለም አቀፍ የመድኃኒት ክትትል ፕሮግራም ሙሉ አባል በመሆን ተመዝግባለች።

# ወጣቶችን በሥነ-ምግባር ለማነጽ የሚረዳ ‹‹ቴኳንዶ ለሁሉም›› የተሰኘ መጽሐፍ ለንባብ በቃ

ሒርሞን ፍቃዱ

አዲስ አበባ፡- ወጣቶችን በስፖርትና በሥነ-ምግባር ለማነጽ የሚረዳ ‹‹ቴኳንዶ ለሁሉም›› የተሰኘ መጽሐፍ ለንባብ በቃ።

በግሎባል ማስተር አረፈዓይኔ ወልደሚካኤል የተፃፈው ‹‹ቴኳንዶ ለሁሉም›› የተሰኘው መጽሐፍ ሰሞኑን ተመርቋል።


ግሎባል ማስተር አረፈዓይኔ ለኢፕድ እንደተናገሩት፤ መጽሐፉ ከማርሻል አርት ዓይነቶች አንዱ የቴኳንዶ ጥብብ ላይ ያተኮረ ነው።

ስፖርታዊ ጥበቡ የተለያዩ ዘዴዎችን በመጠቀም ራስን ለመከላከል እና ለማጥቃት በብዙ ልምድ የሚሠራ ጥንታዊ የትግል ዓይነት ነው ብለዋል።

ስፖርቱ በተለይ በአሁኑ ጊዜ ወላጆች ለልጆቻቸው የሚመርጡት መሆኑን ጠቁመው፤ ምክንያቱ ደግሞ አካላዊ ብቃት ከማነፅ በተጨማሪ የመንፈስ ጥንካሬ የሚያላብስ፣ ሕግ እና ደምብ አክባሪ እንዲሆኑ የሚያደርግ ነው ሲሉ ገልጸዋል።

የቴኳንዶ ጥበብ መማር በዋናነት በሥነ ምግባር የታነፀ ትውልድ ለማፍራት ጠቀሜታው የጎላ መሆኑን የጠቀሰው ግሎባል ማስተር አረፈዓይኔ፤ ሀገር በዘርፉ ተወዳድራ አሸናፊ እንድትሆን ትልቅ ሚና እንዳለው አመላክተዋል።

በአሁኑ ወቅት ሀገራችን የወርልድ ቴኳንዶ ተወዳድራ




ኦሎምፒክ ላይ መግባቷን በማስታወስ፤ ይህንን ውጤታማ ለማድረግ በዚህ ዘርፍ ታዳጊዎች ለማፍራት በዕወቀት የታገዘ ሥልጠና ለመስጠት መጽሐፉ ዋነኛ መሆኑን አስረድተዋል።

የማርሻል አርት ጥበብ በአምስት እንደሚከፈል ጠቅሰው፤ ቴኳንዶ፣ ኢንተርናሽናል ቴኳንዶ፣ ውሹ፣ ካራቴ እና ጁዶ በመባል እንደሚታወቁ አመላክተዋል። መጽሐፉ በዋናነት የቴኳንዶ ጥበብ እና መመሪያ እንዲሁም መርሆችን በዝርዝር እንደያዘ ተናግረዋል።

ከመመሪያዎች መካከል ለሀገር ታማኝ መሆን፣ ወላጆችህን መታዘዝ እና ሌሎች ጠቃሚ እሴቶች የሚገነባ ሲሆን፤ ማንኛውም የቴኳንዶ ተማሪ ትምህርቱ ሲያጠናቅቅ ከሚፈፅመው ቃለ መሐላ መካከል የበለጠ ሠላማዊ ዓለም እገነባለሁ የሚል እንደሚገኝበት አብራርተዋል።

በመጽሐፉ ምርቃት ላይ የአዲስ አበባ ከተማ ወርልድ ቴኳንዶ ኃላፊ አቶ ጥላሁን ዋሲሁን እንዳሉት፤ የቴኳንዶ ጥበብ የአካል ጥንካሬ ብቻ ሳይሆን የመንፈስ ጥንካሬ እና የፈጠራ ችሎታ ለማሳደግ ይረዳል፡፡ በተለይ ታዳጊዎች በመልካም ባሕሪ ለማነፅ ከትምህርታቸው ጎን ለጎን ወደዚህ ሥልጠና ቢገቡ ከራሳቸው አልፈው ሀገራቸውን የሚያስጠሩበት አጋጣሚ ሊፈጥሩ ይችላሉ ብለዋል።

መጽሐፉ ላይ እንደተጠቀሰው የቴኳንዶ ጥበብ በማንኛውም ዕድሜ ለሚገኙ ሰዎች በደረጃቸው ሊማሩት የሚችሉ ጥበብ መሆኑን ለማስረዳት የሚችል መሆኑን ተናግረዋል፡፡ በመሆኑም ለመማር ሀሳቡ ያላችሁ ወይም ልጆቻቹ ለማስተማር ብትፈልጉ ቅድሚያ የንድፈ ሀሳብ ዕውቀት ለማግኘት መጽሐፉ እንደሚረዳ ገልጸዋል።

# "የሠላም ካውንስሉን...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

መንገሻ (ዶ/ር)፤ ካውስሉ ባቀረበው ጥሪ መሠረት የክልሉ መንግሥት ችግሮችን በሠላማዊ መንገድ ለመፍታት ጥሪው በፍጥነት ተቀብሏል ብለዋል፡፡

የክልሉ መንግሥት ግጭት አውዳሚ መሆኑን በማመን ለሠላም ከመቼውም ጊዜ በላይ ዝግጁ መሆኑን በመግለጽ፤ ችግሮችን በጠረጴዛ ዙሪያና በድርድር ለመፍታት ከመቼውም ጊዜ በላይ ዝግጁ መሆኑን ተናግረዋል።

በክልሉ የተካሄደውን የሠላም ኮንፍረንስን ተከትሎ የታጠቁ ኃይሎች ወደ ሠላማዊ መንገድ እየገቡ እንደሚገኝ ጠቅሰው፤ ከቀበሌ ጀምሮ በተካሄደው የሠላም ኮንፍረንስ በርካታ ሠላም ወዳድ የኅብረተሰብ ክፍል መሳተፉን ገልጸዋል፡፡

የኮንፈረንሱ ተሳታፊዎች ከሠላም ሁሉም አካላት ተጠቃሚ መሆናቸውን አንስተዋል ያሉት ኃላፊው፤ ሠላም በክልሉ እንዲሰፍን ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ጫካ ያሉትና መንግሥት ወደ ድርድር ሊገቡ ይገባል የሚል ጥያቄ ቀርቧል ብለዋል።

ኅብረተሰቡ ከሠላም መደፍረስ ጋር ተያይዞ መንቀሳቀስ እንዳልቻሉና ንብረታቸው እየተዘረፈ መሆኑን መግለጻቸውን ጠቅሰው፤ የሕክምና፣ የትራንስፖርት፣ የንግድ እና ትምህርት እንቅስቃሴዎች ላይ ጫና እንደፈጠረባቸው ተሳታፊዎች መናገራቸውን ገልጸዋል።

ከሠላም የሚጠቀመው መላው ማኅበረሰቡ መሆኑን በመግለጽ፤ ለሠላም ቁርጠኛ በመሆን ሠላምን የሚያደፈርስና ለድርድር ዝግጁ የማይሆንን ኃይል እናወግዛለን የሚሉ ሀሳቦች ማንሳታቸውን አስረድተዋል።

የሠላም እጦት በርካታ ቦታዎች ላይ ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ተፅዕኖ አሳድሯል ማለታቸውን ገልጸው፤ ለሀገር ግንባታ ከፍተኛ ሚና የሚጫወቱ ወንድም፣ እህቶችና ልጆች የጦርነቱ ሰለባ ሆነዋል ሲሉ መናገራቸውን ገልጸዋል።

የሠላም ኮንፈረንስ ተሳታፊዎች መንግሥትና የታጠቁ ኃይሎች ወደ ድርድር መምጣት እንዳለባቸው መግለጻቸውን የተናገሩት ኃላፊው፤ የክልሉ መንግሥት ለሠላም ድርድሩ ፈቃደኛ በመሆኑ ታጥቀው የሚንቀሳቀሱ ኃይሎች ፍቃደኛ ሲሆኑ የድርድር ሀሳቡን እንደሚያቀርብ ጠቁመዋል።

የክልሉ መንግሥት ማንኛውም የታጠቀ ኃይል ወደ ሠላም ከመጣ አስፈላጊውን ድጋፍ እንደሚያደርግ በመግለጽ፤ ሀገር የሚገነቡ ታዳጊ ሕጻናትና ወጣቶች ስለሀገር እድገትና ተወዳዳሪነት ማሰብ እንጂ የጥይት ድምፅ እየሰሙ ማደግ የለባቸውምና ችግሮችን በሠላማዊ መንገድ ለመፍታት ዝግጁ ነን ብለዋል።

ኅብረተሰቡ ከምንም በላይ እድገትንና ለውጥን እንደሚፈልግ ጠቅሰው፤ ለሠላም እኔ ነኝ መታገል ያለብኝ በሚል የሚደርስበት ተፅዕኖ ተቋቁሞ ጥረት እያደረገ እንደሚገኝ ገልጸዋል።

ሕዝቡ በጫካ ታጥቆ የሚንቀሳቀስ ማንኛውም ኃይል ሠላም እንዲሰፍን ወደ ሠላማዊ ድርድር መምጣት አለባቸው ማለታቸውን ገልጸው፤ መንግሥትም የሕዝቡን ጥያቄ ተቀብሎ እጁን ዘርግቶ እየጠበቀ እንደሚገኝም ገልጸዋል።

በመጨረሻም አዲሱ ትውልድ ሀገር መረከብ የሚችለው መማርና መመራመር የሚችሉት ሠላም ሲኖር መሆኑን በመግለጽ፤ በጫካ ታጥቀው የሚንቀሳቀሱ ወንድሞች ሁሉም ነገር በጦርነት ሊፈታ አይችልምና አንድ ሆነን ከችግር መውጣት አለብን ሲሉ ጥሪ አቅርበዋል።

# ዓለም አቀፍ የገንዘብ ድርጅቶች...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የፋይናንስ ችግር የለበትም ያሉት አምባሳደሩ፤ ነገር ግን የክፍፍል ችግር በስፋት ይስተዋላል። ከሁለት በመቶ የማይበልጠው ባለጸጋ አብዛኛውን የዓለም ሀብት ጠቅልሎ ይዟል። ሠላም ለማስፈን፤ ስደተኛን፤ ሽብርተኝነትና የፖለቲካ ቀውስን ለመቀነስ የዓለም ሀብት ለሁሉም በእኩል መዳረስ እንዳለበት ገልጸዋል።

በዕዳ ጫና ጀርባቸው የጎበጡ በርካታ ታዳጊ ሀገሮች አሉ ያሉት ሚኒስትሩ፤ የዕዳ ጫናው ቃል በመግባት ብቻ ሳይሆን በተግባር ሊቃለል ይገባል ነው ያሉት።

የዘላቂ ልማት ግቦችን ለማሳካት ፋይናንስ አስፈላጊ ነው ያሉት አምባሳደር ታዬ፤ የዘላቂ ልማት ግቦች ውጤታማ እንዲሆኑ ዕዳ ማቃለልን በሚመለከት ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ድርጅቶችና ዓለም አቀፍ መንግሥታት ማሰብ አለባቸው ብለዋል።

ሀገራት ዕዳቸው ካልተቃለለ ከሚያገኙት ዓመታዊ ገቢ ውስጥ አብዛኛውን ለዕዳ መክፈል ስለሚያውሉት አዲስ የሥራ ዕድልና ልማቶችን ለማፋጠን እንደሚቸገሩ ገልጸዋል።

አራተኛው ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ለልማት ጉባኤ በስፔን ይካሄዳል ያሉት ሚኒስትሩ፤ ኢትዮጵያና ሜክሲኮ ቅድመ ዝግጅት ስብሰባ እንዲያዘጋጁ ተመርጠዋል። ሁለተኛው የቅድመ ዝግጅት ስብሰባ በሜክሲኮ ይካሄዳል ተብሎ ይጠበቃል። ስፔን በሚካሄደው አራተኛ ጉባኤ ላይ አዳዲስ የፋይናንስ እይታዎች እንደሚኖሩም ጠቁመዋል።

ከዚህ በፊት ቃል ተገብተው ያልተተገበሩትን በመገምገም ቀጣይነት ያለው እድገትን ማረጋገጥ ይገባል። የዘላቂ ልማት ግቦች በልገሳ ሳይሆን በቁርጠኝነት የሚመጣ መሆን እንዳለበት ገልጸዋል።

የዓለም እድገትና ፀጥታ ተከፋፍሎ የዓለም ፖለቲካና ኢኮኖሚ እድገት ወደ ተፈለገው ግብ ሊደርስ አይችልም ያሉት ሚኒስትሩ፤ የዓለምን ችግር ለማቃለል የታዳጊ ሀገሮችን የልማት ጥያቄ የበለጸጉ ሀገሮች ማድመጥ አለባቸው። የታዳጊ ሀገሮች የሀገር ውስጥ አዳዲስ ፈጠራዎችና ተነሳሽነቶች ለእድገት ዋና ቁልፍ በመሆናቸው ለጋሽ ድርጅቶች ያለ ደጅ መጥናት የገንዘብ ድጋፍ ማድረግ እንዳለባቸው አስገንዝበዋል።

እንደ አምባሳደር ታዬ ገለጻ፤ ኢትዮጵያ ከከተማ ልማት፣ ከዲጂታል ቴክኖሎጂ፣ ከኢነርጂ ልማት፣ ከትምህርትና ከጤና ልማት አንጻር አዳዲስ የፈጠራ ሥራዎችን እየተገበረች ነው። በቴክኖሎጂ ዘርፍ የተደረገው ግስጋሴ ትልቅ ውጤት እየተገኘበት ነው። ይህን ተሞክሮ ለታዳጊ ሀገሮች ማጋራት ያስፈልጋል።

ከሁሉም በላይ የኢትዮጵያ የአረንጓዴ ዐሻራ በተግባር ለውጥ ያመጣና ጎልቶ የሚታይ መሆኑን ገልጸው፤ ይህም ከምግብ ዋስትናን ከማረጋገጥ ባሻገር የሥራ ዕድል የሚፈጥሩ ናቸው ብለዋል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ምክትል ዋና ፀሐፊ አሚና መሐመድ በበኩላቸው እንደገለጹት፤ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ሥርዓቱ አካታችና ለሁሉም እንዲሆን እየተሠራ ነው። የተረጋጋና ለሁሉም እኩል የሆነ ዓለምን ለመፍጠር በጋራ መልማት አስፈላጊ ነው። ታዳጊ ሀገሮች የዘላቂ ልማት ግቦችን እንዲያሳኩ የፋይናንስ ችግር ሊቀረፉላቸው እንደሚገባም አንስተዋል።

የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ለሁሉም በእኩልነት ይሠራል ያሉት ምክትል ጸሐፊዋ፤ የዓለምን የገንዘብ ፍሰት ማስተካከልና ውጤታማ ዓለም አቀፍ የታክስ ሥርዓት መገንባት እንደሚገባ ገልጸዋል።

እንዲሁም ወጣቶችን ሴቶችን በመደገፍና የአየር ንብረት ለውጥን በመከላከልና ዘላቂ ልማትን ማረጋገጥ እንደሚገባ አመልክተዋል።

# "ዘመናዊ የፖለቲካና...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

የኢትዮጵያ ችግር የፖለቲካ ነው። የፖለቲካ ችግሩም በተፎካካሪ ፓርቲዎችና በገዢው ፓርቲ መካከል መነጋገርና መወያየት ባለመኖሩ የተከሰተ ነው ያሉት አቶ ደስታ፤ ይህንን ችግር ለመቅረፍ ውይይቱ በጎ ሚና አለው። ይህን መሰል ውይይትም አጠናክሮ መቀጠል እንደሚገባ ተናግረዋል።

በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተመዘገቡ የፖለቲካ ፓርቲዎች የውይይቱ ተሳታፊ መሆናቸውን የገለጹት አቶ ደስታ፤ በውይይቱ የፖለቲካ ምሕዳሩን የሚያሰፉ ጉዳዮች ላይ ምክክር ተደርጓል። በዚህም ተፎካካሪ ፓርቲዎች በሠላማዊ መንገድ ሥልጣን የሚይዙበትን ዘመናዊ የፖለቲካ ሥርዓት ለመገንባት በሚያስችሉ ሁኔታዎች ላይ ውይይት ተደርጓል ብለዋል።

በሀገሪቷን ሠላምና ደህንነት እንዲሁም በሕግ የበላይነት፣ በሁሉን አቀፍ ሀገራዊ ምክክር፣ በመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ፣ በቀጣናዊና ዓለም አቀፋዊ ዲፕሎማሲ፣ በኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች እና በሌሎች ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ሰፊ ውይይት መደረጉንም ገልጸዋል።

እንደ አቶ ደስታ ዲንቃ ገለፃ፤ በፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል የመነጋገር ባሕልን በማጎልበት ሀገራዊ ችግሮችን በጋራ የመፍታት ልምድ ተጠናክሮ መቀጠል አለበት። በጋራ ሀገራዊ ጉዳዮች ላይ ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር ለመወያየት መንግሥት እያሳየ ያለውን ቁርጠኝነት አድንቀው፤ ፓርቲዎችም ለዚሁ ዝግጁ መሆን አለባቸው ሲሉ ተናግረዋል።

የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ የውይይት መድረኮች ሀገራዊ ችግሮችን በጋራ ለመፍታትና የዳበረ የዴሞክራሲ ሥርዓት ለመገንባት ጥሩ መሠረት የሚሆኑ መሆናቸውንም ገልጸው፤ የተካሄደው ውይይት በፖለቲካ ፓርቲዎች በጋራ የሚፈቱትን በጋራ ለመፍታት የሚያስችል መሆኑን ጠቅሰዋል።

ለሕዝብና ለትውልድ ተስፋ የሚሆኑ ዓላማዎችን በመሰነቅ ኢትዮጵያን ከችግር ለማውጣት በጋራ ልንቆምና ልንሠራ ይገባል ያሉት አቶ ደስታ፤ ይህ የፖለቲካ ፓርቲዎች የመመካከር ሂደት አዲስ የፖለቲካ ባሕል ጅማሮ በመሆኑ በቀጣይም በመነጋገር ሀገራዊ ጥቅሞችን ማስጠበቅ፣ ችግሮችን መፍታትና መልካም ነገሮችን ማስቀጠል የሚቻል መሆኑን ተናግረዋል።

# ያደጉ ሀገራት...

ከ1ኛ ገጽ የዞረ

እ.አ.አ በሰኔ ወር 2025 በስፔን ለሚካሄደው አራተኛው የተባበሩት መንግሥታት የዓለም አቀፍ የፋይናንስ ኮንፈረንስ አጀንዳ ማሰባሰቢያ ኮንፈረንስ ትላንት በአዲስ አበባ መካሔድ ጀምሯል።

በጉባኤው ላይ ንግግር ያደረጉት የኢፌዴሪ ገንዘብ ሚኒስትር አቶ አሕመድ ሺዴ፤ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት በማደግ ላይ ያሉ ሀገራትን ታሳቢ ያደረገ ፍትሐዊ የፋይናንስ ሥርዓት ሊዘረጉ እንደሚገባ በመግለጽ፤ በአሁን ወቅት ዓለም በሰው ሠራሽና ተፈጥሯዊ አደጋዎች ምክንያት ባልተረጋጋ የፋይናንስ ሥርዓት ውስጥ ትገኛለች ብለዋል።

እንደ አቶ አሕመድ ገለፃ፤ እንደ ኢትዮጵያ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት በፖለቲካ አለመረጋጋት፣ በኮቪድ-19፣ በአየር ንብረት ለውጥ፣ በዓለም ሀገራት ፍትሐዊ ባልሆነ የፋይናንስ ሥርዓትና በሌሎች በተለያዩ ምክንያቶች የፋይናንስ ሥርዓታቸው አደጋ ውስጥ ወድቋል።

በዚህም ፍትሐዊ የፋይናንስ ሥርዓት ተግባራዊ ማድረግ አስፈላጊ ነው፤ ለዚህም አዳዲስ የፋይናንስ የፈጠራ ሀሳቦችን በማመንጨት፣ የግሉን ዘርፍ በማነቃቃት ችግሮችን መፍታት እንደሚያስፈልግ የጠቆሙት አቶ አሕመድ፤ ለዚህ ደግሞ ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ተቋማት በማደግ ላይ ያሉ ሀገራትን ታሳቢ ያደረገ ወጥ አሠራር መዘርጋት እንዳለባቸው ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ የባሕልና የታሪክ ሀብታም ሀገር መሆኗን የጠቀሱት የገንዘብ ሚኒስትሩ፤ በመሠረተ ልማት ማስፋፋት፣ በድህነት ቅነሳ፣ በትምህርት፣ በጤናና በሌሎችም ዋና ዋና የልማት ግቦች ላይ አበረታች ውጤቶችን እያስመዘገበች መሆኑን ተናግረዋል።

በየዓመቱ በሚሊዮን የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን እየተሳተፉበት የሚገኘው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐግብር የግብርናውን ዘርፍ በማጠናከር፣ የሥራ ዕድል በመፍጠር፣ ምቹ የአየር ንብረት እንዲኖር በማድረግ የራሱን አስተዋፅዖ እየተወጣ ይገኛል ነው ያሉት።

እ.አ.አ በ2015 ኢትዮጵያ የሦስተኛውን ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ልማት ኮንፈረንስ መሰናዶ በተሳካ ሁኔታ ማስተናገዷን አስታውሰው፤ የኮንፈረንሱ ተሳታፊዎች ሀሳባቸውን በማዋጣትና ዛሬን በመጣር የተሻለ ነገን መፍጠር እንዳለባቸው አንስተዋል።

በመድረኩ መክፈቻ ላይ በቪዲዮ ኮንፈረንስ ንግግር ያደረጉት የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ዋና ጸሐፊ አንቶኒዮ ጉተሬዝ በበኩላቸው፤ ዓለም በከፍተኛ የፋይናንስ ችግር ላይ እንዳለችና በዓለም ላይ በጂኦ ፖለቲካ ልዩነት ላይ የተመሠረተ ፍትሐዊ ያልሆነ የፋይናንስ ፍሰት መፈጠሩን ተናግረዋል።

የተበላሸውን የዓለም የፋይናንስ ሥርዓት ለማስተካከል ካደጉና ባለፀጋ ከሆኑ ሀገራት ብዙ ይጠበቃል ያሉት ዋና ጸሐፊው፤ በቀጣይ የሚደረገው ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ጉባኤ ይህን የተዛባ የፋይናንስ ሥርዓት መስመር እንደሚያሲይዝ እምነት እንዳላቸው ገልጸዋል።

እየተከናወነ በሚገኘው የአጀንዳ ማሰባሰብ መድረክ በርካታ የመፍትሔ ሀሳቦች እንደሚጠበቁ የገለጹት ዋና ፀሐፊው፤ በስፔን የሚካሄደው ዓለም አቀፍ ጉባኤ ንግድና ኢንቨስትመንትን በማጠናከር የተሳለጠ የፋይናንስ ሥርዓት ለመዘርጋት የጎላ አበርክቶ ይኖረዋል ነው ያሉት።

እንዲሁም በሦስተኛው ዓለም አቀፍ የፋይናንስ ለልማት ኮንፍረንስ ለፀደቀው የውሳኔ ሀሳብ እና ለ2030 የዘላቂ ልማት ግቦች መሳካት ተግባራዊ እንቅስቃሴ ሊኖር እንደሚገባም አሳስበዋል።

# ርዕሰ አንቀፅ

## ከግጭት ምዕራፍ ወደ ሠላምና ልማት ምዕራፍ ለመሸጋገር!

እንደ ሀገር በ2016 በጀት ዓመት ለማከናወን የታቀዱ ተግባራት ተቋጭተው፤ የ2017 በጀት ዓመት ተግባራትን ወደመከወን ተገብቷል። በዚህ ሂደት ኢትዮጵያ የበዙ መልካም ተግባራትን ከውና ከፍ ያለ ውጤትና ስኬትን ማስመዝገብ የቻለችበት የበጀት ዓመትን ማሳለፏን ከተለያዩ ሪፖርቶች መገንዘብ ተችሏል።

በአንጻሩ፣ ከበዛው ስኬትና ውጤቷ ባሻገር የሚገለጹ፣ እዚህም እዚያም የሚታዩ ማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ችግሮች በሠላም መደፍረስ ታጅበው ሂደቱን ለመገዳደር መሞከራቸው አልቀረም። እንደ አጠቃላይ ግን ስኬት ያለ ድካም፤ ውጤት ያለ ፈተና አይገኝምና፤ በፈተና ውስጥም ሆና ሀገር ከፍ ያለ አፈጻጸምን ማሳየት ችላለች።

እንደ ሀገር በተገኘው ውጤት ውስጥ የክልሎች ሚና ከፍ ያለ ነው። በዚህ መልኩ በስኬትም ሆነ በፈተና ሂደቷ ውስጥ በሁለቱም ገጾቿ ቀድመው ከሚገለጹ ክልሎች መካከል አንዱ የኦሮሚያ ክልላዊ መንግሥት ሲሆን፤ ክልሉ ባካሄደው ዓመታዊ ጉባኤው ላይ የዓመቱን አፈጻጸም እና የቀጣይ እቅዱን ከስኬትም ከፈተናዎቹም አኳያ ቃኝቶ አሰምቷል።

በወቅቱ የክልሉ ርዕሰ መስተዳደር አቶ ሽመልስ አብዲሳ ለጨፌው ባቀረቡት የ2016 በጀት ዓመት እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት በርካታ ጉዳዮችን አንስተዋል። በማብራሪያቸው እንዳነሱትም፤ በክልሉ 123 ነጥብ 15 ቢሊዮን ብር ገቢ ተሰብስቧል፤ በመስኖ ስንዴ 102 ነጥብ ሁለት ሚሊዮን ኩንታል ምርት ተገኝቷል፤ በሩዝ ልማትም ቢሆን በ2015/16 ምርት ዘመን 32 ሚሊዮን ኩንታል ምርት ማግኘት የተቻለበት ነው።

ከዚህ በተጓዳኝ በኢንቨስትመንት 148 ቢሊዮን ካፒታል ያስመዘገቡ ሦስት ሺህ 757 ፕሮጀክቶች ውሳኔ ተሰጥቶባቸዋል። ዘጠኝ ሺህ 654 የመጠጥ ውሃ ፕሮጀክቶች በሕዝብ ተሳትፎ፣ በመንግሥትና በልማት ድርጅቶች ትብብር ተሠርተው ተጠናቀዋል። ከአራት ሺህ በላይ ቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤቶች ተገንብተዋል፤ ለ2 ነጥብ 3 ሚሊዮን ዜጎች ቋሚ የሥራ ዕድል ተፈጥሯል። ሙስናን ለመከላከል በተሠራው ሥራም ሊመዘበር የነበረ አምስት ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ማዳን ተችሏል።

ከዚህ ሁሉ ስኬት በተጓዳኝ ደግሞ ሠላም የክልሉ ትልቁ ተግዳሮት የነበረ ሲሆን፤ የልማት ሥራዎቹ ስኬታማ ተግባር የተከናወነውም በዚሁ ፈተና ውስጥ ተሆኖ ነው። ይሁን እንጂ፣ ከልማት ተግባራቱ ጎን ለጎን የክልሉን ሠላም ለማረጋገጥ ዘርፈ ብዙ ተግባራት ተከናውነዋል። በተለይ የክልሉን ሕዝብ ሁሉን አቀፍ ተጠቃሚነት ያረጋገጡ የሠላምና የልማት ሥራዎች በመከናወናቸው ሠላምን ለማረጋገጥ በተከናወነ የሕግ ማስከበር ሥራ ውጤት ተገኝቷል። እየተወሰደ ባለው ሠላምን የማስከበር ርምጃ ብሎም መንግሥት ለሠላም ባደረገው ተደጋጋሚ ጥሪ በመታገዝ በርካታ የሸብር ቡድኑ አባላት እጅ የሰጡ ሲሆን፤ እጅ የሰጡና የአሸባሪው ሸኔ አባላትን ወደ ኅብረተሰቡ በቀጥታ ከመቀላቀል ይልቅ በሦስት ዙር የተሐድሶ ሥልጠና ወስደው ወደ ኅብረተሰቡ እንዲቀላቀሉ ተደርጓል።

ይሄን መሰሉ በልማቱም፣ በሠላሙም እየተገኘ ያለው ውጤት ደግሞ ለ2017 በጀት ዓመት እንደ ሀገር በተቀመጠው ግብ ውስጥ ክልሉም ከፍ ያለ ሚናውን ይወጣ ዘንድ የበኩሉን አበርክቶ የሚያደርግ ነው። በመሆኑም ከልማት አኳያ፣ በ2017/18 የምርት ዘመን በበልግና በመኸር 12 ነጥብ አራት ሚሊዮን ሄክታር በማልማት ከ379 ሚሊዮን ኩንታል በላይ ምርት ለማግኘት፤ ከገቢን አኳያም 206 ነጥብ 08 ቢሊዮን ብር ገቢ ለመሰብሰብ ውጥን ተይዟል።

ከዚህ በተጓዳኝ፣ ለሦስት ነጥብ አራት ሚሊዮን ዜጎች የሥራ ዕድል ይፈጠራል፤ በሺዎች የሚቆጠሩ ትምህርት ቤቶች ይገነባሉ፤ ደረጃቸውም እንዲሻሻል ይደረጋል። በሺህ ኪሎ ሜትሮች የሚለካ የአዳዲስ መንገድ ግንባታ እና ጥገና ተግባራት ይከናወናሉ። በኢንቨስትመንት ዘርፉም ቢሆን 200 ነጥብ ስድስት ቢሊዮን ብር ካፒታል ያስመዘገቡ 30 ሺህ ፕሮጀክቶችን በመቀበል ለአንድ ነጥብ ሰባት ሚሊዮን ዜጎች የሥራ ዕድል ለመፍጠር ታቅዷል።

ይሄን መሰል የሕዝቦችን ሁለንተናዊ ተጠቃሚነት የሚያረጋግጡ ተግባራት ታቅደው ሊሠሩም ሆነ ኅብረተሰቡን ተጠቃሚ ሊያደርጉ የሚችለው ግን ከሁሉም በፊት ሠላም ሲኖር እና ሁሉም ዜጋ ለዚህ ተግባር ንቁ ተባባሪም፣ ተሳታፊም ሲሆን ነው። በመሆኑም እንደ ሀገርም ሆነ እንደ ክልል የታቀዱ ተግባራት እንዲሳኩ ከታሰበ ሁሉም ኃይል ለሠላም ቅድሚያ ሰጥቶ መሥራት ይጠበቅበታል።

ለዚህም ነው፣ የክልሉ ርዕሰ መስተዳድር ለጨፌው ሪፖርት ባቀረቡበት ወቅት፣ "የታጠቁ ኃይሎች ከጥፋት መንገድ ተመልሰው የግጭትን ምዕራፍ መዝጋት አለብን" ሲሉ ጥሪ ማቅረባቸው። ምክንያቱም፣ ልማቱ ሊፋጠንና የሚፈለገው ብልጽግና እውን ሊሆንና የዜጎችን ሁሉን አቀፍ ተጠቃሚነት እውን ማድረግ የሚቻለው፤ ሁሉም ከግጭት አስተሳሰብና ተግባር ወጥቶ፤ ለጋራ ልማት፣ ለጋራ ሠላም እና ለሁለንተናዊ ብልጽግና እውን መሆን ሲሠራ ነው። በመሆኑም ከግጭት ምዕራፍ ወጥቶ ወደ የጋራ ሠላምና ልማት ምዕራፍ መሸጋገር የ2017 በጀት ዓመት የሁሉም ተግባር ሊሆን ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስፈጻሚ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

ኢሜል ፦ epa@press.et

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፦ 011 126 4200

Email:- wendweson.shimelis@press.et
wendwesonshimelis@gmail.com

**የዜና ማዕከል ዋና አዘጋጅ**

ወርቁ ማሩ

Email:- workumaru2@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ኃይሉ ሣህለድንግል
- እስማኤል አረቦ
- ቦጋለ አበበ

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

ቴሌግራም - 097- 608-47-07 - Press

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ** ፦ ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


# ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የችግኝ ተከላው ባሕል ለእንክብካቤውም ይዋል!

ትንሳኤ አበራ

የሀገራችን የክረምት ወራት ከሌሎች ወራት የተለየ ገጽታ አላቸው። የዝናብ ወቅት እንደመሆኑ ጭጋጉ፣ ዝናቡ፣ ጭቃው፣ ብርዱ፣ ወዘተ አስፈሪ ወቅት ቢያደርጋቸውም፣ ከሀገራችን የምግብ ዋስትና ማረጋገጫ የማምረት ሥራዎች ከሚካሄድባቸው ወቅቶች መካከል ዋናው የሆነው የመኸር እርሻ ሥራ የሚካሄድባቸው ናቸው።

የግብርና ሥራው ደግሞ በሰብል ልማት ላይ ብቻ የታጠረ አይደለም፤ የደን ልማት ሥራዎችም በስፋት ይካሄዳሉ። እንደ ክረምት ከችግኝ ጋር የሚስማማና የሚግባባ ወቅት ባለመኖሩ ችግኞችን ለመትከልም ለመንከባከብም ይህ በእጅጉ ይመረጣል። በዚህ ወቅት በተለይ አርሶ አደሮች በችግኝ ተከላው በስፋት ሲሠሩ ኖረዋል።

ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ደግሞ ይህ ታላቅ ሥራ ለአርሶ አደሩ ብቻ የተተወ አይደለም። ከተሜውም በከተሞች አካባቢ፣ ለአረንጓዴ ስፍራ በተተዉ ክፍት ቦታዎች እንዲሁም ወደ ገጠር ጭምር በስፋት በመግባት የችግኝ ተከላውን በከፍተኛ ርብርብ በስፋት እያካሄደ ይገኛል።

የችግኝ ተከላ ሥራን ፊትም ኅብረተሰቡ ክረምቱን ተከትሎ በተበታተነ መልኩ በየፊናው ሲያከናውነው የኖረ ሲሆን፣ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ግን በተቀናጀ መንገድ የሚከናወን ሀገራዊ ተግባር ተደርጓል። ክረምትና የችግኝ መትከል ሥራ የማይነጣጠሉ ሆነው በአንድነት እየታዩ ናቸው፤ ይህም የችግኝ ተከላውን ባሕል ማድረግ አስችሏል። የችግኝ ተከላው በተቀናጀና በተናበበ መልኩ በመንግሥት የተለየ ትኩረት ተሰጥቶት «የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር» የሚል መጠሪያም ተሰጥቶት በሃገር አቀፍ ደረጃ ለአምስት ዓመታት የተካሄደበት ሁኔታም ይህንኑ ያመለክታል።

በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) አነሳሽነት በሃገር አቀፍ ደረጃ በ2011 ዓ.ም. የተጀመረው ይህ የአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር፣ መላ የኢትዮጵያ ሕዝብን ከዳር እስከ ዳር በማንቀሳቀስ እያሳተፈ በመሆኑ ባለፉት አምስት ዓመታት ከ32 ነጥብ አምስት ቢሊዮን በላይ ችግኞችን መትከል አስችሏል።

በዚህ የችግኝ ተከላ በአንድ ጀንበር በተተከሉ የችግኞች መጠን በሀገሮች የተያዙ ክብረ ወሰኖችን ለመስበር በማቀድ ጭምር በተከናወነ የችግኝ ተከላ ከአቅድም በላይ ከ350 ሚሊዮን በላይ ችግኞችን መትከል የተቻለበት ሁኔታም እንደነበር ይታወቃል። በዚህም ምንም እንኳ በተለያዩ ምክንያቶች ሪኮርዱ ባይመዘገብም፣ በአንድ ጀምበር የ66 ሚሊዮን ችግኞችን በመትከል ተይዞ የነበረውን የዓለም የክብረ ወሰን ለመስበር መሠራቱ ይታወሳል።

መላ ዓለም በአየር ንብረት መዛባት በድርቅ፣ በጎርፍ፣ በአውሎ ነፍስ፣ በሰደድ እሳት እና መሰል የተፈጥሮ አደጋዎች ተጋላጭ ለመሆኑ በግንባር ቀደምትነት ከሚጠቀሱ ምክንያቶች አንዱ የተፈጥሮ ሀብት መራቆትና የደን መጨፍጨፍ ነው። ኢትዮጵያም የዚህ ችግር ዋናዋ ገፈት ቀማሽ መሆኗ ይታወቃል።

ይህን ዓለምን ስጋት ላይ እየጣለ ያለውን የአየር ንብረት ለውጥ ለመቋቋም አይነተኛ መፍትሔ ተብለው ከተቀመጡ ተግባሮች አንዱ ችግኝ በመትከል የደን ሀብትን ወደ ቀድሞ ይዞታው መመለስ ነው። ኢትዮጵያም አረንጓዴ ኢኮኖሚን በመገንባት ሂደት ያለች ሀገር እንደመሆኗ ለደን ልማት ትኩረት በመስጠት «አረንጓዴ ዐሻራ» በሚል የችግኝ ተከላ መርሐ ግብር በየዓመቱ በቁርጠኝነት እየተገበረች ትገኛለች።

በ2011 ዓ.ም በተጀመረውና ላለፉት አምስት ዓመታት በተከታታይ በተካሄደው በዚህ መርሐ ግብርም 32 ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኞችን መትከል ተችሏል። ዘንድሮም ሰባት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል አቅዳ ወደ ትግበራ ገብታለች።

ጥናቶች እንደሚያሳዩት፤ በአንድ ወቅት የኢትዮጵያ የደን ሽፋን 40 በመቶ ነበር። ይህን የደን መመናመን ለማስቆምና ወደ ቀድሞ ይዞታው ለመመለስ በአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብር ከፍተኛ በተከናወነ ተግባር ከፍተኛ ለውጥ ማምጣትም ተችሏል። በዘንድሮው የአረንጓዴ ዐሻራ ቅድመ መክፈቻ መርሐ ግብር ላይ የኢትዮጵያ የደን ሽፋን በ2011 ዓ.ም. ከነበረበት 17ነጥብ2 በመቶ ወደ 23ነጥብ6 በመቶ ከፍ ብሏል በሚል ከተገለጸው መረዳት እንደሚቻለውም በልማቱ ከፍተኛ ለውጥ ማሳየት እየተቻለ መሆኑን ነው።

በ2013 ዓ.ም «ኢትዮጵያን እናልብስ »በሚል መርሐ ግብርም በሃገር አቀፍ ደረጃ 6 ቢሊዮን ችግኞችን ከመተከላቸው በተጨማሪ የችግኝ ተከላው ክፍለ አሕጉራዊ እንዲሆን ለማድረግ ጭምር ተሠርቶበታል። በዚህም አንድ ቢሊዮን ችግኞች ለጅቡቲ፣ ሶማሊያ፣ ኤርትራ፣ ሱዳን፣ ደቡብ ሱዳንና ኬንያ መሰጠቱም ይታወሳል። ሀገሪቱ ችግኝ በመትከል ለዓለም ጭምር እያበረከተች ያለችው አስተዋፅዖ በዓለም አቀፍ ደረጃ ጎልቶ እየታየ ከመሆኑም በተጨማሪ በችግኝ ተከላው ለሌሎች ሀገሮች ተምሳሌት እንድትሆን እያደረጋትም ይገኛል።

ዘንድሮም 7ነጥብ5 ቢሊዮን ችግኞችን ለመትከል የተያዘውን እቅድ ለማሳካትም የችግኝ ተከላው ሥራ ተጠናክሮ ቀጥሏል። እስከ አለፈው ሳምንትም ከአራት ቢሊዮን በላይ ችግኞች መተከላቸውን መረጃዎች አመልክተዋል።

የሚተከሉ ችግኞች ብዛት ብቻ ሳይሆን እየጨመረ ያለው የችግኞች የፅድቀት ምጣኔ እየጨመረ ነው። መረጃዎች እንደሚጠቁሙት የችግኞች የፅድቀት ምጣኔ በአማካኝ 80 በመቶ ያህል ደርሷል። ለእዚህ ደግሞ የኅብረተሰቡ ሚና ከፍተኛ መሆኑ ይታመናል።

አንዳንድ ወገኖች ግን ይህ የፅድቀት ምጣኔ ዝቅተኛ ነው ሲሉ ይገልጻሉ። እርግጥ ነው በተከላው እየታየ ያለው ርብርብ በእንክብካቤው ብዙም አይታይም። ለእዚህ ዋና ምክንያት ተደርጎ የሚወሰደው ደግሞ ለችግኞች ሊደረግ የሚገባው እንክብካቤና ክትትል በሚፈለገው ልክ አለመሆኑ ነው። ይህም ችግኞቹ በእንክብካቤ ማግኘት ያለባቸውን እንዲያገኙ በማድረግ ላይ ብዙ አልተሠራም በሚል ይገለጻል።

አንዳንድ ተቋማት ካልሆኑ በስተቀር አብዛኞቹ የተከሏቸውን ችግኞች መለስ ብለው እያዩ አለመሆናቸው፣ የተከላውን ያህል በእንክብካቤው የሚደረግ ርብርብ ብዙም አለመታየቱ ሲታሰብም ለእንክብካቤው የተከላውን ያህል ትኩረት አልተሰጠም ማለት ይቻላል።

አስተያየቱ ሊወሰድ ይገባዋል። ለችግኞች የሚደረገው አንክብካቤ በሚፈለገው ልክ መሆን ከቻለ ችግኝ ከመትከል ባልተናነሰ በችግኝ እንክብካቤም ለአረንጓዴ ዐሻራ መርሐ ግብሩ አስተዋፅዖ ማድረግ እንደሚቻል ይታመናል።

«ችግኝና ሕጻን ልጅ አንድ ናቸው» እንደሚባለው ሁለቱም በጥሩ ሁኔታ እንክብካቤ ከተደረገላቸው ለቁም ነገር እንደሚደርሱ ሁሉ ለችግኝ ተከላው የሚደረገው እንክብካቤ ተጠናክሮ መቀጠል ይኖርበታል።

በችግኝ እንክብካቤው ላይ ለመሥራት ከሚያስፈልጉት መካከል አንዱ ችግኞችን በመንከባከብ ላይ ያሉ ተቋማትን ተሞክሮ አውጥቶ ማሳየት ይጠቅማል። ጥቂትም ቢሆኑ በእዚህ በኩል ጥሩ እየሠሩ ያሉ ተቋማት አሉ። ይህን ተሞክሮ ማስፋት ይገባል።

ችግኞች ከተኮተኮቱ፣ ከሰውና እንስሳት ንክኪ ከተጠበቁ፣ በበጋ ወቅት ደግሞ ውሃ የሚያገኙበት ሁኔታ ከተፈጠረ የፅድቀት መጠናቸው ብቻ አይደለም የሚጨምረው፤ እድገታቸውም የተፋጠነ ይሆንና ለተፈለገው ዓላማም ቶሎ መድረስ ይችላሉ።

ባለፉት ዓመታት የተተከሉና በአሁኑ ወቅት እየተተከሉ የሚገኙ በብዙ ቢሊዮን የሚቆጠሩ ችግኞችን በሙሉ ለመንከባከብ ከፍተኛ ጥንቃቄ ማድረግም ያስፈልጋል። የእንክብካቤ ሥራው በዘመቻ ሊፈጸም አይችልም። በባለሙያ፣ በሠለጠኑ አካላት መፈጸም ይኖርበታል። ይህን ማድረግ ይገባል።

ችግኞቹን በሙሉ ውሃ ማጠጣትና መኮትኮት ሊያስቸግር ይችላል። በአቅራቢያችን ያሉትን ችግኞች ግን ውሃ በማጠጣት ጭምር መንከባከብ ይኖርብናል። ሌሎች በሰፊና በሩቅ ቦታዎች ላይ የተተከሉትንና የሚተከሉትን ውሃ ማጠጣትና መኮትኮት ይቸገራል። እነሱን ደግሞ ከሰውና እንስሳት ንክኪ በመጠበቅ ብቻ የፅድቀት መጠናቸውን ማሳደግ እንዲሁም ለተፈለገው ዓላማም ቶሎ እንዲደርሱ ማድረግ ይቻላል።

አንዳንድ ተቋማት እንደሚያደርጉት ሥራ አጥ ወጣቶችን አደራጅቶም ይሁን በሌላ መልኩ ችግኞችን መንከባከብ ሁኔታም ይኖራል። በእዚህም ወጣቶቹንም ሃገርንም ተጠቃሚ ማድረግ ይቻላል። ወጣቶች በወል ቦታዎች የተተከሉ ችግኞችን በመንከባከብ፣ በስፋራው የሚገኙ እንደ ሣር ያሉትን ደግሞ እንዲጠቀሙ ማድረግም ሌላው ለችግኝ እንክብካቤው የሚጠቅም ተግባር ነው።

እያንዳንዱ የአረንጓዴ ዐሻራ ተሳታፊ እንዲሁም መርሐ ግብሩን የሚመሩ ከላይ እስከታች ያሉ አካላት ሕዝቡ ዐሻራውን ያሳረፈባቸው ችግኞች የት ደረሱ? ለችግኞቹስ ምን አይነት እንክብካቤ እየተደረገላቸው ነው? በማለት በየጊዜው መጠየቅና እንክብካቤው በአግባቡ እንዲከናወን ማድረግም ይገባል።

ዘንድሮ 7ነጥብ 5 ቢሊዮን ችግኖችን ለመትከል የተያዘው መርሐ ግብር እንዳለፉት ዓመታት ሁሉ ስኬታማ እንዲሆን የሁሉም ዜጋ የነቃ ተሳትፎ ያስፈልጋል፤ ይህ ተሳትፎ ችግኞችን ከመትከልም እንዲሻገር በማድረግ ለእንክብካቤ ትኩረት ሰጥቶ መሠራትም ይኖርበታል። ይህ ከሆነ እስከ አሁን የተከልናቸውም ሆኑ አሁን የምንተክላቸው ችግኞች አድገውና ለተፈለገው ዓላማ ደርሰው የምናይበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም።

ቸር እንሰንብት።

# ነፃ ሃሳብ

# "አረንጓዴ ዐሻራ - ነገን ዛሬ መሥራት"

**በትረ ሙሴ (መልከ ኢትዮጵ)**

ኢትዮጵያውያን በአንድነት ከሚከውኑት ሀገራዊ ትላልቅ ተግባራት መካከል የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር አንዱ ነው:: በየዓመቱ የክረምት መግቢያ ሰሞን ላይ በጠቅላይ ሚኒስቴር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) መሪነት ብዙሃንን ባነቃነቀ የተሳትፎ ንቅናቄ ችግኝ እንተክላለን:: ዘንድሮም በተመሳሳይ መልኩ ለአንድ አላማ፣ በአንድ የመከርንበት የአረንጓዴ ዐሻራ ማስጀመሪያ መርሀ ግብር በጠቅላይ ሚኒስቴር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ንግግር ተጀምሯል::

‹የምትተክል ሀገር የሚያጸና ትውልድ› በሚል መሪ ሃሳብ የተጀመረው የዘንድሮው የግሪን ሌጋሲ ንቅናቄ እንዳለፈው ጊዜ ዓለም አቀፋዊነትን በተላበሰ መልኩ ርምጃ የጀመረ ነው:: የመሪ ሃሳቡ ዋና ዓላማ ኃላፊነትን ከሀገር ፍቅር ጋር ማስቀጠል የሚል አንድምታ ያለው ሲሆን በተለይ ደግሞ ወጣቱ አውቆና ተረድቶ ከአባቶቹ እዳን ሳይሆን ምንዳን፣ ጥላቻን ሳይሆን አንድነትን፣ ድህነትን ሳይሆን ልማትን የሚወርስበትን መድረክ ለማመቻቸት ጭምር ነው::

ሀገርና ትውልድ ተነጣጥለው የማይታዩበት አረንጓዴ ዐሻራ በመሪ ሃሳቡ በኩል መጪውን ከአሁኑ ጋር አስተሳስሮ በማስቀጠል ረገድ ሚናው ላቅ ያለ ነው:: ከዛሬ ወደ ነገ የሚሸጋገርን ትውፊት በቅብብሎሽ ለማስቀጠል እንደምቹ አጋጣሚ የተፈጠረ ከሕዝብ ለሕዝብ የሆነ እሳቤ ነው:: ትውልዱን ከኃላፊነት ጋር ለሀገር የሚታትርበትን ሞራል ለመፍጠር አቅም የሚሆን፣ በድርቅና በበረሃማነት በድህነት የምትታወቅን ሀገራችንን በልምላሜ ለመግለጥ ቆርጦ የተነሳ ንቅናቄ ነው::

ጠቅላይ ሚኒስቴር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) በንግግራቸው "እኛ ላይ እዳ ወድቋል ይሄን እዳ ለልጆቻችን ማውረስ የለብንም" ብለዋል:: በንግግራቸው ላይ እዳ ተብሎ የተገለጸው ከመትከልና ከማጽደቅ ጋር ኃላፊነቱን በአግባቡ የማይወጣውን ትውልድ ነው:: ሀገር በኃላፊነት እዳን በሚቀይር አእምሮና ልብ የተማገረች ናት:: በሥራችን ኃላፊነታችንን መወጣት ካልቻልን ከጥቅማችን ጉዳታችን ያመዝናል:: ያለፈውን ትተን ስለመጪው ብናወራ ዛሬ ላይ እየተከልናት ያለችው አንድ ችግኝ መጪውን ትውልድ ነፃ ከማውጣትና እኛንም በታሪክ ከማስመስገን አኳያ አስተዋጽኦዋ የላቀ ነው::

ሰው የልማዱ ባሪያ ነው፣ ልምምድ በቀላሉ የምንገላገለው አይደለም:: ዛፍ እየቆረጥን በመጥፎ ልማድ መጥተናል:: ይሄ ልምምድ በጎ በሆነ በህብረት ልምምድ የሚጠፋ ነው ያሉት ጠቅላይ ሚኒስቴር ዐቢይ አሕመድ አክለውም ከ40 በመቶ ወደ ሶስት በመቶ የደን ሽፋን መውረዳችንን ከአጉል ልምምዳችን ጋር አያይዘው ተናግረዋል:: በእውነቱ ይሄ በጣም የሚያሳዝን ነው:: ዓለም ቀስ በቀስ እየጠፋች ነው ያልኩትና ብሔራዊ ሙዚየም ያስተዋልኩት የድሮና የዘንድሮ የተፈጥሮ ምስል ይሄን እውነታ የሚያረጋግጥ ሆኖ አግኝቼዋለሁ::

ወደ መፍትሔው መማተር ከዚህ ዓይነቱ አደጋ ለመውጣት ብቸኛ መንገዳችን ነው:: ጠቅላይ ሚኒስቴር ዐቢይ አሕመድ እንዳሉት "እኚህ መጥፎ ልምዶች የሚሻሩት እንደ አረንጓዴ ዐሻራ ባሉ ማህበራዊ ልምምዶች ነው:: የአየር ንብረት ለውጥ በስብሰባ አይቀየርም:: በወሬ፣ በሱፍ ለባሾች አይቀየርም:: እጃቸውን ጠቅለው በሚተክሉ የሚቀየር ነው:: መትከል ምግብም ነው፣ ውበትም ነው:: የምንተክለው ምግባችንን ነው:: የምንተክለው ውበታችንን ነው:: ባለፉት ጊዜ በመትከላችን ከሀገር ውስጥ ፍጆታ እስከ ውጭ ኤክስፖርት ድረስ ተጠቃሚዎች ነበርን" ሲሉ ተናግረዋል::

በዚህ ዓመት ካለፈው ልቀንና ገዝፈን ሰባት ነጥብ አምስት ቢሊዮን ችግኝ ለመትከል ተበስሯል:: ዛሬን ነገ መሥራት ማለት በዚህ ዓይነቱ ሕዝባዊ ንቅናቄ የሚገለጽ ነው:: ሰዎች ወደ ጫካ መሄዳቸው ቀርቶ ጫካን ወደ ሰዎች ማምጣት የዚህ ትውልድ ሚና እንዲሆን ከእያንዳንዳችን የሚጠበቅ ተግባር መሆኑ ሌላው በማስጀመሪያ መርሀ ግብሩ ላይ የተበሰረ ጉዳይ ነው:: ተፎካካሪ ፓርቲዎች፣ ሽማግሌዎች፣ ወጣቶች፣ ሕፃናት የራሳቸውን ዐሻራ በማሳረፍ የአረንጓዴ ዐሻራ የሚናው ተሳታፊ መሆን ይጠበቅባቸዋል ሌላው የአደራ መልዕክት ነው::

**ጊዜው በአረንጓዴ ዐሻራ እንደ ሁልጊዜያችን ታሪክ የምንሰራበት ነው። የታሪካችን መነሻ አሁን ቢሆንም መድረሻው ነገ ሆኖ ለእያንዳንዳችን አደራ ተሰጥቶናል**

ዛፍ ከመቁረጥ መጥፎ ልማድ ዛፍ ወደመትከል የብዙሃን ልምምድ መሸጋገር የትውልዱ ኃላፊነት እንዲሆን የሁላችንም ምኞት ነው:: በዚህ አቅጣጫ ካልሆነ ዋጋ እያስከፈሉን ካሉ ልምምዶቻችን መራቅ አንችልም:: የአየር ንብረት ለውጥ የዓለም ችግር ነው:: ራሳችንን የምንታደገው ሌሎችን በመጠበቅ ሳይሆን የድርሻችንን በመወጣት ነው:: ተክለን ስናጸድቅ ኃላፊነታችንን እየተወጣን ነው:: በኩራትና በመንደላቀቅ የምንኖርባትን አዲሲቷን ኢትዮጵያ እየፈጠርን ነው:: ይሄ እውነታ በአንድ ቃል ቢገለጽ ነገን ዛሬ መሥራት የሚለውን ይሆናል:: አረንጓዴ ዐሻራ ነገን ዛሬ ከመሥራት ሌላ በምንም አይገለጽም:: የዛሬ ኃላፊነቶቻችን ነገን ነፃ የምንወጣባቸው፣ እንደ ሥጋት ከፊታችን የተጋረጡን የአየር ንብረት ለውጦችን የምናልፍባቸው፣ በርሃማነትንና የአየር መዛባትን የምናስተካክልበት ከምንም በላይ ደግሞ ራሳችንን ከተፈጥሮ አደጋ ስጋት ጠብቀን ምቹ ከባቢን የምንፈጥርበት ነው::

አንዳንድ አጋጣሚዎች ዋጋቸው በተመን አይለካም:: የአረንጓዴ ዐሻራ ንቅናቄም ከተመን በላይ የሆነ በሕይወት የሚሰላ አላማ ያለው ዓለም አቀፍ እውነታ ነው:: የምንተክለው ላለመሞት ነው:: የምናጸድቀው በአረንጓዴ ዐሻራ ቀጣይነት ያለው የመኖር ዋስትናን ለማረጋገጥ ነው:: ለተፈጥሮ ሞልታና ተትረፍርፋ የተሰጠችን ቢሆንም በእኛ እንዝህላልነት አናዋን አስቀርተናታል:: ምድር አረንጓዴ ሰማይ ደግሞ በሰማያዊ ቀለም አጊጠው በፈጣሪያቸው በኩል የተቸሩን ስጦታዎቻችን ናቸው:: ሆኖም ግን እነዛ ጥንተ መልኮች አሁን ላይ የሉም::

ዓለም መልስ ካጣችለት አሁናዊ ጉዳይ አንዱ የአየር ንብረት ለውጥ ነው:: መነሻው ብዙ ቢሆንም ማዳረሻው ግን የአረንጓዴ ዐሻራ ንቅናቄ ነው:: ዛፍ ስንተክል ደልቶን አይደለም እንደ ሀገር መጪ ጫናዎቻችንን ለማስቀረት እንደ ዓለም ደግሞ ለሌሎች የመኖር ዋስትና ለመሆን ነው:: ያለፈውን ትተን ሰሞነኛውን የአየር ንብረት ሁኔታ ብንመለከተ በዓለም ላይ በዚህ ሳምንት ብቻ በድንገተኛ ሙቀት በርካቶች ሕይወታቸውን አጥተዋል:: ይሄ ችግር እኛ ሀገር ያለመግባቱ ዋስትና ከዚህ ቀደም የተከልናቸው ዛፎች አስተዋጽኦ ነው::

በመንግሥት በኩል ወደ ትውልዱ የወረደው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር አላማው ለመጪው ትውልድ እዳን ያለማውረስ ግብግብ ነው:: ባለፉት አራትና አምስት ዓመታት ውስጥ ሥነ ምህዳርን ከመጠበቅ ጎን ለጎን የአየር ንብረት ስጋትን የመከትንበት ሁኔታ አለ:: ብዙ ሀገራት የምንሰማቸው የተፈጥሮ አደጋዎች እኛ ጋ ያልቀረቡት ትላንትና በወሰድነው የአረንጓዴ ዐሻራ ርምጃ መሆኑ ማረጋገጫ የሚያሻው ጉዳይ አይደለም:: ከዚህ ጋር በተያያዘ ጠቅላይ ሚኒስቴር ዐቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ‹አሁን ዛሬ የማንተክል፣ የማንከባከብ ከሆነ ከጥቂት ዓመታት በኋላ አፈር እየተሸረሸረ፣ እየተወሰደ ከሆነ ጊዜ በኋላ እንትከል ብንል እንኳን ለመትከያ የሚሆን አፈር አናገኝም:: የተቆረጠ ዛፍ በአጭር ዓመት ውስጥ ራሱን ይተካል የተወሰደ አፈር ግን በአንድ ሺ ዘመናት ውስጥም ራሱን ማደስ አይችልም› ሲሉ ዛፍ የመትከላችንን አንገብጋቢ ምክንያት አስረግጠው ተናግረዋል::

ዛሬ ላይ ካልተከልን ነገ ላይ እንደ ሰው የመኖራችን ጉዳይ ጥያቄ ውስጥ ይገባል:: ይሄ ምርምር የማያስፈልገው ግልጽ እውነታ ሆኖ በሁላችንም የሚታመን ነው:: ዓለም በተፈጥሮ ስጋት በኩል ቀስ በቀስ እየጠፋች ነው:: ይሄ ጥፋት የሚያገግመው ደግሞ በአረንጓዴ ዐሻራ በኩል ነው:: ልክ አንድን ቀዳዳ ጥብቆ በመርፌ ጥፎ የማሳመር ያክል የተፈጥሮ ሽንቁርም በአረንጓዴ ዐሻራ በኩል የሚታከም ነው:: ካልሆነ ሽንቁሩ ሰፍቶ መጣፍ ወደማይችልበት ደረጃ ይደርስና ህልውናችንን ተረት ያደርገዋል:: ሳይቀጠል በቅጠል እንዲሉ የዛሬ ትጋቶቻችን ለነገ መልስ እየሰጡ ያሉ ተግባሮች እንደሆኑ መታወቃቸው ወደፊት እንድንገፋ የሚያደርገን ነው::

ዛፍን በኃላፊነት መትከልና ማጽደቅ ከመንግሥት ዓመታዊ እቅዶች መካከል አንዱ ሆኖ እየተተገበረ ይገኛል:: በቀጣይም በጀት ተመድቦለት በስፋትና በጥራት እንቅስቃሴው እንደሚቀጥል እየተነገረ ይገኛል:: ከዓመት ዓመት በኃይልና በብርታት መልኩን እየቀየረ የመጣው ይሄ ንቅናቄ በአጭር ጊዜ ውስጥ ፍሬ አፍርቶ ግቡን እንደሚመታ እሙን ነው:: ከአረንጓዴ ዐሻራ ጋር የተገናኙ ማህበራዊ ልምምዶች በአንድ ድንጋይ ሁለት ወፍ ዓይነት ጥቅም ያላቸው ናቸው:: የመጀመሪያው ትውልዱን ከእዳ ማላቀቅ ነው:: በዚህ ውስጥ አብረው የሚነሱ ለውጥና እድገትን መሠረት ያደረጉ ሀገራዊ ትሩፋቶችም አብረው ይነሳሉ:: ትውልዱ በኃላፊነት ዛፍ ሲተክል መጪውን ጊዜ በተስፋ ከመቃኘት ጎን ለጎን ለሕይወት ዋስትና የሚሆኑ ዐሻራዎችን እያስቀመጠ ይሄዳል::

ሁለተኛው ከምንተክላቸው ዛፎች የምናገኘው በረከት ነው:: በረከቱ ብዙ ዓይነት ነው:: አካባቢን ከመጠበቅ፣ አፈር እንዳይሸረሸር ከማድረግ፣ የዝናብ ወቅትን ከመቆጣጠር፣ በርሀማነትን ከመከላከል፣ ክረምትና በጋ ወቅቱን ጠብቆ እንዲመጣ በማድረግ፣ የአፈር ለምነትን በመጠበቅ፤ ንጹህ አየርን ለመተንፈስ... በረከቱ ብዙ ነው:: ከዚህ ጋር ተያይዞ የሚነሳው ሌላው ፋይዳ ምቹና ለጤና ተስማሚ የሆነ አካባቢን መፍጠር ነው:: በዚህ እንቅስቃሴ ላይ እንደ መንግሥት ትልቁ ኃላፊነት በተፈጥሮ አደጋ በኩል ከስጋት ነፃ የሆነች ኢትዮጵያን መፍጠር ነው:: በዚህም እየተሳካልን ይገኛል::

እንደ ሀገር የምንተክለው እዳን ለትውልዱ ላለማውረስ ብቻ አይደለም በድህነት ላይ እንደቁምጥና ከሚነሳው የአየር ንብረት ስጋት ለመዳን ነው:: ተፈጥሮ ዛፍ ሰጥቶናል የእኛ ኃላፊነት የተሰጠንን መንከባከብ ነበር ፤ ሆኖም ያንን ባለማድረጋችን ካለፈው እዳ ተቀብለን ለመጪው እዳን እያስተላለፍን ነው:: አሁናዊ ትግላችን ይሄንን የውርስ እዳ ለማስቀረት ነው:: በገዛ ጥፋታችን መንከባከብ ብቻ የሆነውን ተግባራችንን ወደመትከል አሸጋግረነዋል:: አሁን ላይ ካልተከልንና ካልተንከባከብን ለም አፈሮቻችን በመሸርሸራቸው እህል ማብቀል የማይችሉበት ደረጃ ላይ ይደርሳሉ:: ይሄ መሆኑ ርሀብና ድህነት ስር እንዲሰድ መንገድ የሚጠርግ ነው::

የአረንጓዴ ዐሻራ መርሀ ግብር በአንድ አቅጣጫ ብቻ የሚተረጎም አይደለም:: ሁሉም ቦታ ያለ ሁሉንም የሚነካ የህልውና ጉዳይ ነው:: ለዛም ነው መንግሥት ሰፊ ሽፋን ሰጥቶ ባልተቋረጠ መልኩ እያስኬደው ያለው:: የዛሬ ትጋቶቻችን የመጪው ዘመን ፍሬዎቻችን ናቸው:: ኃላፊነትን ከሀገር ፍቅር ጋራ ባጣመረ መልኩ እየተከልን መንከባከብ ነገም የሚቀጥል የቤት ሥራችን ነው:: ኃላፊነቱን በአግባቡ የማይወጣ ትውልድ በትችትና በወቀሳ የሰላ ከመሆኑ በላይ በስንፍና የታወቀ ነው:: እንደ አረንጓዴ ዐሻራ ያሉ ሁሉን አቀፍ እንቅስቃሴዎች ደግሞ በኃላፊነት ተጀምረው የሚያበቁ ናቸው:: የምትተክል ሀገር የሚያጸድቅ ትውልድን ነው የምትፈጥረው:: የሚያጸድቅ ትውልድ ደግሞ በእዳ ሳይሆን በምንዳ የሚያምን ነው::

የዘንድሮው ሕዝባዊ ተሳትፎ እንዳለፈው ጊዜ ከሀገር አልፎ አህጉራዊና ዓለም አቀፋዊ ሽፋን ያለው ሆኖ ለብዙዎች የመነቃቃት መንፈስን የሚፈጥር እንደሚሆን ይታመናል:: ያለፉት የተሳትፎ ዓመታቶች ከሀገር ልቀው መላውን ዓለም ያነጋገሩ እንደነበሩና በርካቶችን ለትጋት የቀሰቀሱ እንደሆኑ ይታወሳሉ:: ዘንድሮም ካለፈው በተሻለ ሕዝባዊ ተሳትፎና እንቅስቃሴ መሰል ድሎችን ለመጎናጸፍ ዝግጅቱ በሁሉም ዘንድ ይሁንታን አግኝቷል::

አረንጓዴ ዐሻራ የሕይወት ደም ስር ነው:: ዛፍ ከሕይወት ጋር የተሰላ የመኖርና ያለመኖር ጉዳይ ነው:: የምንተነፍሰው አየር ከአረንጓዴ ቀለም መንጭቶ ወደሳንባችን የሚገባ ከዛም ተመልሶ የሚወጣ ዓይነት ተፈጥሮ ያለው ነው:: ስንተክል ሕይወት እየተከልን ነው፣ እድሜ እየቀጠልን ነው:: ስናጸድቅ ህልሞቻችንን እውን እያደረግን ነው:: ከዚህ ወዲያ ያለው ድርጊት ለሕይወት እምብዛም ዋጋ የሌለው ነው::

ዛፍና ሕይወትን በአንድ ተፈጥሮ መስለን ብንናገር አካልና ነፍስ ይሆናሉ:: አካል ያለ ነፍስ ነፍስም ያለ አካል ማደሪያ የለውም:: ይሄ እንደ ግለሰብና እንደ ማህበረሰብ የሰፋ አድማስ ያለው እሳቤ ነው:: እንደ ሀገር ሲሆን ደግሞ የት ድረስ እንደሆነ መረዳቱ ቀላል ነው:: አረንጓዴ ዐሻር መነሻው ሀገር እና ትውልድ መፍጠር መሆኑ እምብዛም የሚያጠያይቅ ባይሆንም ከሞራልና ከያገባኛል ጋር ሲሆን ደግሞ ዋጋው የዛኑ ያክል የላቀ ነው::

ሀገር ከዛ ወደዚህና ከዚህ ወደዛ ቅብብሎሽ ናት:: ቅብብሎሹን የተሳለጠ የሚያደርገው ደግሞ የትውልዱ ኃላፊነትን የመሸከም አቅም ነው:: በበሳል ምሬትና ሁሉን ባቀፈ የጋራ ተልዕኮ ሀገር የትውልድ ቅብብሎሽ ናት ስንል እንዲህ ባለው እሴት በኩል መሆኑ አይጠፋንም:: ችግኝ ስንተክል ትውልድ እየተከልንና መጪውን ጊዜ ብሩህ እያደረግን እንደሆነ ለሁሉም የሚታመን እውነታ ነው:: ዓለም በግሎባል ዋርሚንግ እና በተያያዥ ችግሮች በምትሰቃይበት በዚህ ጊዜ መጪውን ቃኝቶ ቀድመን መዘጋጀታችን አርቆ አሳቢነታችንን የሚያሳይ ነው:: ለዚህ ደግሞ መንግሥት በኩር ተወዳሽ ሲሆን ሕዝብ ተከታዩ ተመስጋኝ ይሆናል::

በተያያዙና በተባበሩ እጆች በተከልናቸውና ባጸደቅናቸው ችግኞች አዲስ ክስተት ፈጥረን ከዓመት ዓመት መነጋገሪያ ሆነናል:: ኢትዮጵያውያን በአንድ ስንነሳ ዓለምን ማስደነቅ እንደምንችል በተለያዩ አጋጣሚዎች አስመስክረናል:: ጊዜው በአረንጓዴ ዐሻራ እንደ ሁልጊዜያችን ታሪክ የምንሰራበት ነው:: የታሪካችን መነሻ አሁን ቢሆንም መድረሻው ነገ ሆኖ ለእያንዳንዳችን እንደ አደራ ተሰጥቷል:: ‹የምትተክል ሀገር የሚያጸና ትውልድ› እንደመሪ ሃሳብ ብዙሃነትን ያቀፈ፣ ከዛሬ ወደነገ የሚሻገር አንቂና አሳታፊ መሆኑ እሙን ቢሆንም ከዚህ በላይ ጎልቶ የሚነሳው ደግሞ አላማ መር በሆነ ንቅናቄ ከእዳ ወደምንዳ፣ ከነውጥ ወደለውጥ፣ ከንቅቅፍ ወደትቅቅፍ አሻጋሪ መሆኑ ነው:: ቸር ሰንብቱ!

ኢኮኖሚ

# ሳይንስና ቴክኖሎጂ

# የደን ሀብት መረጃን በቴክኖሎጂ መምራት

**ወርቅነሽ ደምሰው**



ኢትዮጵያ በአንድ ወቅት በደን ሀብት የተሸፈነች እንደነበረች መረጃዎች ይጠቁማሉ። የደን ሽፋኗ 40 በመቶ ከነበረበት ሁኔታ መረዳት የሚቻለውም ይህንኑ ነው። ሀገሪቱ ይህ ሀብቷ ባለፉት ዘመናት ሲጨፈጨፍና ሲራቆት ቆይቷል። በዓመት እስከ 100 ሺ ሄክታር የተፈጥሮ ደን ሲመነጠር፣ በሰደድ እሳት ሲወድም መቆየቱን ጥናቶች ያሳያሉ። በዚህም የተነሳ ይህን ሀብቷን ከማጣቷ ባሻገር ለድርቅ ለአካባቢ መራቆት ለበረሃማነት ለምግብ እጥረት እና ለደህነት ስትጋለጥ ኖራለች።

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ይህንን ለመቀልበስና አረንጓዴ ኢኮኖሚን ለመገንባት የአካባቢ ጥበቃ እና የደን ልማት ሥራዎች በስፋት እየተሰሩ ይገኛሉ። በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ (ዶክተር) አነሳሽነት ልዩ ትኩረት ተሰጥቶት በተጀመረው «የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር»ም በሀገር አቀፍ ደረጃ በብዙ ቢሊዮኖች የሚቆጠሩ ችግኞች እየተተከሉ ነው።

በደን ልማት ሥራ ውስጥ እነዚህን ችግኞች መትከል ብቻ በቂ አይደለም፤ የደን ሀብቶቹ ያሉበትን ሁኔታ ለማወቅ የሚያስችል በቴክኖሎጂ የታገዘ የመረጃ ሥርዓት እንዲኖር ማድረግ ያስፈልጋል። እንደ ሀገርም የደን ሀብቱን ለማወቅና ጥቅም ላይ ለማዋል የሚረዱ በቴክኖሎጂ የታገዘ የመረጃ ሥርዓት እንዲኖር የሚያስችሉ ሥራዎች እየተሰሩ ናቸው።

በዘንድሮው የአረንጓዴ ዐሻራ መርሃ ግብር ማስጀመሪያ ሥነ ሥርዓት ላይ እንደተገለጸው፤ የሀገሪቱ የደን ሽፋን በ2011 ዓ.ም ከነበረበት 17 ነጥብ 2 በመቶ አሁን ላይ ወደ 23 ነጥብ 6 በመቶ በጥናት ተረጋግጧል። ጥናቱ የደን ልማት ዓለም አቀፍ ልምድ ካላቸው ተቋማት ጋር በመሆን በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የአየር ንብረት ለውጥ ኮንቬንሽን መስፈርት መሠረት የተሰራና ተቀባይነት ያገኘ ነው። የደን ሽፋኑ ሲሰላ ዘመኑ የደረሰበት ዘመናዊ የቴክኖሎጂ ጥቅም ላይ የዋሉ መሆኑም ተመላክቷል።

ወርቁ ዘውዴ (ዶክተር) የደን ዘርፍ ተመራማሪና አስተማሪ እንዲሁም የደንና የሳተላይት መረጃ አማካሪ ናቸው። እሳቸው እንደሚሉት፤ ቴክኖሎጂ ለሁሉም ሥራ ያስፈልጋል። ዛሬ ላይ መገናኛ ብዙኀን ሳይቀር የሚጠቀሙበት የሳተላይት መረጃ አየር ላይ ባሉ ሳተላይቶች ተሰብስቦ ለመረጃነት የሚያገለግል ነው። የደን ሀብቱም እንዲሁ በቴክኖሎጂ የታገዘ መረጃ ያስፈልገዋል።

ሦስት ዓይነት የደን ሀብት መረጃዎች አሉ። የመጀመሪያው ከመሬት የሚሰበሰበ መረጃ ነው። ሁለተኛው በአውሮፕላን ወይም በዌብ የሚሰበሰብ ሲሆን፤ ሦስተኛው ከሳተላይቶች የሚገኝ መረጃ ነው።

እነዚህም መረጃዎች የሚገኙበት በሦስት ዓይነት ዘዴዎች ነው፤ አንደኛው ኦፕቲካ (በፀሐይ ብርሃን ተጠቅሞ) መረጃ የሚሰበሰብ ነው። ሁለተኛው ደግሞ የራዲዮ ሞገድ( ዌብ) ተጠቅሞ መረጃ የሚሰበሰብ ነው። ሦስተኛው የራሱን ብርሃን ለቆ ከሚመለሰው ብርሃን ከሚያገኘው መረጃ የሚሰብሰብ ነው።

እነዚህ ሦስት የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ደኑን ለማወቅ የሚያስችሉ ናቸው የሚሉት ተመራማሪው፣ መረጃ መሰብሰቢያዎቹ ደኑ የት ቦታ ይገኛል? በዚያ ቦታ ላይ ምን ያህል መጠን ያለው ደን አለ? ያለውስ ደን ምን ይመስላል? የሚሉትን ለማወቅ የሚረዱ ናቸው ሲሉ ያስረዳሉ።

ደኑን ምን ይመስላል? በሚለው የዛፉን ቁመት፣ ቅርንጫፍና ስብጥር ማወቅ እንደሚቻል ገልጸው፤ ይህም የራሱን ብርሃን በመልቀቅ ከሚሰበሰበው መረጃ እንደሚገኝ ያመላክታሉ። «ይህም ቴክኖሎጂ የዛፉን ቁመት፣ ቅርንጫፎች፣ ስብጥርና አጠቃላይ ደኑ ክፍተት አለው ወይስ ደፍን ነው ? የሚለውን ለመለየት ይረዳል። መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ስለደን ማወቅ ያለብንን እንዲናውቅ ሊረዱንና በጣም ሊያግዙን ይችላሉ» ብለዋል።

በኢትዮጵያ በየዓመቱ በብዙ ቢሊዮን የሚቆጠሩ ችግኞች ይተከላሉ። እነዚህ ችግኞች በተባለው በቦታ ላይ ስለመተከላቸው በቴክኖሎጂ በመታገዝ ማወቅ ይቻላል የሚሉት ተመራማሪው ፤ አሁን ባለው ቴክኖሎጂ ተጠቅመን ችግኞቹ የተተከሉባቸው ቦታዎች የት ነው? የሚለውን ለማወቅ እና ተከታታይነት ያለው ክትትል እንዲደረግ ያስችላል ይላሉ።

ለአብነት የአረንጓዴ ዐሻራ ከተጀመረበት 2011 ዓ.ም ጀምሮ የተተከሉ ችግኞች በአሁኑ ወቅት የደረሱበት ደረጃ ለመመልከት ያስችላል። ሌላው ቀርቶ የዛፎቹ የካርበን፣ የናይትሮጂን እና ክሎሮፊን መጠን ወይም በቅጠላቸው ውስጥ ያሉትን ንጥረ ነገሮች መጠን መለካትም ይቻላል። በእነዚህ ነጥረ ነገሮች የተነሳ ይዘቱ እያደገ እያደገ ይሄዳል ይላሉ።

ዛፎች በጣም እያደጉ ሲሄዱ አረንጓዴነታቸው እየበዛ መሬት ላይ የሚታየው ክፍተት እየጠፋ ስለሚመጣ ይህ አረንጓዴነት የሚለካበት ቴክኒክም አለ። «ችግኙ ሲተከል መጀመሪያ ክፍት ነበር፤ ከዓመት በኋላ የሆነ ደረጃ ላይ ደረሰ እያለን በዓመታት መለካት ይቻላል። ትንሽ እየቆየ ከሄደ ደግሞ ቴክኖሎጂን በመጠቀም የዛፎቹን ቁመት መለካት ይችላል። ከዚህ አንጻር አረንጓዴ ዐሻራን ልንከታተልባቸው የምችላቸው እድሎች ሰፊ ናቸው» ሲሉ ያስረዳሉ።

ኢትዮጵያ የደን ሀብትን በቴክኖሎጂ ከመምራት አንጻር በኢትዮጵያ በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት እና በምርምር ቦታዎች ቴክኖሎጂ በመጠቀም ሂደት ጥሩ ተሞክሮዎች አሉ የሚሉት ወርቁ (ዶክተር) ፤ ቀደም ብለው የሚታዩት ክፍተቶች ቢኖሩም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ግን የተሻሉ ሥራዎች እየታዩ መሆናቸውን ይጠቁማሉ። ይህም ቢሆን ግን ክልሎችም እየሄዱበት ካለበት ሁኔታ አንጻር ይህንን ቴክኖሎጂ ሙሉ ለሙሉ ተጠቅመው የደኖችን መረጃዎች እየተከታተሉ እየሰሩ ናቸው ለማለት ግን እንደማያስደፍር ይናገራሉ።

በጅምር ደረጃ አበረታች ነገሮች እንዳሉም ጠቅሰው፣ ሙሉ ለሙሉ ተግባር ላይ ውሏል ለማለት እንደሚያስቸግር ይገልጻሉ። እዚህ ላይ የኢትዮጵያ ደን ልማት ክልሎችን ለማገዝ የሚሰራቸው ሥራዎች እንዳሉ ይጠቅሳሉ። «እዚህ ውስጥ እኛም እንደ ባለሙያ አብረን እየሰራን እንገኛለን፤ ጅምሮቹ ጥሩ ናቸው፤ ግን ሌላው ዓለም ከደረሰበት የቴክኖሎጂ እድገት አንጻር ስንመለከት ብዙ ይቀረናል» ብለዋል።

ቴክኖሎጂን በአግባቡ ሥራ ላይ ለማዋል ያሉት ተግዳሮቶች ውስን ናቸው የሚሉት ዶክተር ወርቁ፤ ከእነዚህ ውስጥ አንዱ የባለሙያ እጥረት መሆኑን አንስተዋል። እሳቸው እንዳሉት፤ የደን መረጃ ለመሰብሰብ መሬት፣ ድሮን እና አውሮፕላን እንዲሁም ሳተላይት መጠቀም የግድ ይላል፤ አብዛኞቹ ባለሙያዎች የሳተላይት መረጃ ትንተና ልምዶች አላቸው። ነገር ግን መሬት ለመለካት የራሱን ብርሃን ለቆ የሚለካውን ቴክኖሎጂ በአግባቡ ከማወቅ አንጻር መሻሻል ያለባቸው ነገሮች አሉ። እነዚህ ነገሮች ቢጨመሩ በአቅም ደረጃ በባለሙያ በኩል ብዙ ችግር አይኖርም። ይህ ሥራ የተወሰኑ ባለሙያዎች ብቻ የሚችሉት ይሆንና ዋናው ቦታ ላይ ብዙም ጠንካራ እንዳልሆነ ያመላክታሉ።

ይህንንም በምሳሌ ሲያስረዱ በኢትዮጵያ የደን ልማት ባለሙያዎች እንዳሉ ጠቅሰዋል። የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ሌሎች ባለሙያዎችን በማፍራት ሥራው የበለጠ ተጠናክሮ ወደፊት ሊሰራበት እንደሚገባ ያመላክታሉ።

«በዓለም አቀፍ ደረጃ ከአየር ንብረት ለውጥ፣ ካርበን ልቀት ጋር ተያይዞ ደን ያለበት ሁኔታ እንደሚለይ ይታወቃል። እንደ ሀገር እኛ ደኖች አሉን ብለን ስንናገር ደኖቹ የት ቦታ ነው ያሉት የሚለውን ለመለየትና ለማወቅ በእነዚህ ቴክኖሎጂዎች ተጠቅመው የራሳቸውን ባለሙያ ልከው ነው የሚያረጋግጡት። እኛም ቀደመን ቴክኖሎጂዎችን ተጠቅመን የሰራነው ሥራ መረጃ ከነማስረጃው ይዘን አብረን በመሥራት ማሳየት አለብን። እስካሁን ግን እዚህ ላይ እምብዛም ሥራ አልተሰራም»ይላሉ።

መረጃዎችን በቴክኖሎጂ ታግዞ የመያዙ ሥራ ተጠናክሮ ቀጥሎ አድጎ አብሮ መሥራት ካልተቻለ ወደኋላ መቅረት እንደሚመጣ አመልክተው፣ በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ላይ ያሉትን ጅምሮች ይበልጥ በማሳደግ የተሻለ ደረጃ ላይ መድረስ አለብን ሲሉ ያላቸው እምነት ገልጸዋል።

ይህ ዘመን የቴክኖሎጂ ዘመን እንደ መሆኑ ነፃ ዳታ በቀላሉ ማግኘት ይቻላል የሚሉት ተመራማሪና አማካሪው፣ የባለሙያዎችን አቅም መፍጠርና ዳታው የሚተነተንባቸውን እንደ ኮምፒውተር፣ ሶፍትዌር እና የመሳሰሉት ቁሳቁስ በማሟላት ምቹ ሁኔታዎች መፍጠር እንደሚያስፈልግ አስገንዝበዋል።

ቀደም ሲል እ.ኤ.አ 2008 የናሳ የሳተላይት ዳታ በነፃ ይሁን የሚለው የመጀመሪያ አዋጅ እስከሚታወጅ ድረስ ዳታ የሚገኘው በግዢ ነበር ሲሉም አስታውሰው፣ ምክንያቱም ዋጋው ውድ ስለነበር እንደ ሀገር ገንዘብ ማውጣትና የሳተላይት ዳታ መግዛት ከባድ እንደነበር ገልጸዋል። በአሁኑ ወቅት ይህ ሁሉ ችግር ተቀርፎ የአውሮፓ ህብረት፣ የአሜሪካ እና ሌሎችም ሀገራት ዳታ በነፃ እንዲገኝ የሚያደርግ እድል ተፈጥሯል ሲሉም አስገንዝበዋል።

በተለይ ዳታ ማግኘት ላይ የነበረው ተግዳሮት መቅረፉ ትልቅ ነገር መሆኑን ጠቅሰው፤ አሁን ላይ የባለሙያውን አቅም መፍጠር ይቀራል ይላሉ። «ሥራውን መሬት ላይ በማውረድ መጠቀም ከቻልን ያንን ያህል የሚያስቸግር ነገር ይኖራል ብዬ አላስብም» ሲሉ ወርቁ (ዶክተር) ተናግረዋል።

የኢትዮጵያ ደን ልማት ምክትል ዋና ዳይሬክተር ሞቱማ ቶሌራ (ዶክተር) በበኩላቸው እንደ ሀገር የደን ሀብት መረጃን በቴክኖሎጂ በመታገዝ መሥራት ትኩረት ተሰጥቶት እየተሰራበት መሆኑን ይናገራሉ። በደን ዘርፍ በዓለም አቀፍ ደረጃ ቴክኖሎጂ ትኩረት ተሰጥቶታል። የዘንድሮ የ2024 ዓለም አቀፍ የደን ቀን መሪ ቃል ከፈጠራና ኢኖቬሽን ጋር መሆኑን ለቴክኖሎጂ የተሰጠው ትኩረት ያሳያል ሲሉም ጠቅሰው፣ እንደ ኢትዮጵያ እስካሁን ድረስ ያለው የቴክኖሎጂ ምን ይመስላል። በደን ዘርፉስ ላይ ምን ዓይነት ለውጦች እያመጡ ነው። ዛሬ ላይ የት ነን የሚሉት በደንብ እየተፈተሹ ናቸው ሲሉ ይገልጻሉ።

እሳቸው እንደሚሉት፤ የደን መመንጠርም ሆነ በተለያዩ ቦታዎች ላይ ያለው የተራቆተ ደንን መልሶ እንዲያገግም ለማድረግ የሚረዱ ብዙ ቴክኖሎጂዎች እየመጡ ናቸው። በዘርፉ በየሰዓቱ ያለውን ለውጥ ጭምር ለመቆጣጠር የሚያስችሉ የቴክኖሎጂ ግኝቶች እየታዩ ናቸው። ለምሳሌ በደን ላይ የተከሰተ እሳትም ሆነ ወደፊት ሊከሰት የሚችል እሳትን መቆጣጠር የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎች እየተፈጠሩ መጥተዋል። እነዚህ ቴክኖሎጂዎች በሚቀጥሉት ጊዜ እሳት ሊከሰት የሚችልበት ቦታዎች መለየት ያስችላል።

እዚህ ቦታ ላይ እሳት ተከስቷል እና ገና ሊከሰት ከሆነ በዚህ ጊዜ ውስጥ እሳት ሊከሰት ይችላል ብለው የእሳቱን መከሰት የሚጠቁሙ መረጃዎችን ለሚመለከተው አካል የሚያሳውቅ ይሆናል። አሁን ላይ ቴክኖሎጂውን ከመጠቀሙ አንጻር ጥሩ መሻሻሎች እየታዩ ለውጦች እየመጡ ስለመሆኑ ማሳያ ነው።

በሳተላይት መረጃ በኩልም የአንድ አካባቢን መረጃ በአጭር ጊዜ ውስጥ ወደ ማዕከል የሚላክበት ሁኔታ መኖሩን ገልጸው፤ በዚህም ለውሳኔ የሚመቹ መረጃዎች እየመጡ ውሳኔዎች እየተሰጡ መሻሻሎች ከፍ እያሉ የሄደበት ሁኔታ መኖሩን አመላክተዋል።

ደኖች ለተለያዩ አላማዎች ከቦታቸው ላይ እንዲነሱ ቢደረግ እንኳ አሁን ባለው ቴክኖሎጂ መልሶ የመተካት ሰፊ ሥራን መሥራት ይቻላል ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተር፤ አንድን አካባቢ መልሶ ምቹ አካባቢ ለማድረግ ያሉ ደኖች ቢቆረጡ የተቆረጡት ዛፎች በዘመናዊ ቴክኖሎጂ በመታገዝ መልሶ መትከል እንደሚቻልም ይገልጻሉ። ለአብነትም አዲስ አበባ ከተማን ያነሳሉ። በከተማዋ ምንም ዛፍ ባልነበረባቸው ቦታዎች ሳይቀር በቴክኖሎጂ በመደገፍ በአንድ ዓመት ውስጥ ደን የሚመስል ነገር ለመፍጠር የተቻለበትን ሁኔታ መመልከት እንችላለን ሲሉ ተናግረዋል።

# ወቅታዊ ትንታኔ

# ኢትዮጵያ ስለምን የምግብ ዋስትናዋን ማረጋገጥ ተሳናት ?

**አስቴር ኤልያስ**

የኢትዮጵያ መንግሥት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ የተለያዩ መርሃ ግብሮችን ነድፎ በመንቀሳቀስ ላይ መሆኑ ይታወቃል:: ከዚህ ውስጥ በበጋ መስኖ ላይ የተመሰረተ ሁሉን አቀፍ የግብርና ልማት አንዱ ነው:: በተሻሻሉ የእንስሳት ዝርያ ላይ እየተደረገ ያለ እንቅስቃሴ መኖሩም ይታወቃል:: ይሁንና መሰል የሆኑ የተለያዩ ጥረቶች ቢደረጉም ዛሬም ድረስ የዕለት ጉርስ ማግኘት ያልቻለ የኅብረተሰብ ክፍል መኖሩ የማይታበል ሐቅ ነው::

በተለያዩ ሀገራዊ ፋይዳ ባላቸው ርዕሰ ጉዳዮች ላይ የየዘርፉን ባለሙያ እና የመንግሥት ባለስልጣናትን በመጋበዝ የኅብረተሰቡን ግንዛቤ ከፍ ለማድረግ የውይይት መድረኮችን የሚያዘጋጀው የኢትዮጵያ ሳይንስ አካዳሚ፤ ከሰሞኑም ተመሳሳይ መድረክ አዘጋጅቶ የዘርፉን ምሁራን ያከራከረ ሲሆን፣ ክርክሩ ዋና ትኩረት ያደረገውም በኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና ያለመረጋገጡ መንስኤ ምንድን ነው? ለማሻሻልስ መደረግ ያለበት ምን ዓይነት ተግባር ነው? የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥስ የማን ኃላፊነት ነው? በሚል ዙሪያ ነው::

የዕለቱን መድረክ ሲመሩ የቆዩት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምሁር ፕሮፌሰር ደገፋ ቶሎሳ፣ እንዳሉትም፤ የውይይቱ ዋና ዓላማ ኢትዮጵያ በምግብ ራሷን ሳትችል የቆየችበትን መንስዔ አጠቃላይ ግንዛቤ ለመፍጠር ነው:: ሀገራዊ የምግብ ዋስትና ማሻሻያ ስልቶችን ለመጠቆምም ጭምር ያለመ ነው::

እንደ እርሳቸው ገለጻ ከሆነ፤ ጽንሰ ሃሳቦቹ ሶስት ጉዳዮች ሲሆኑ፣ እነርሱም በምግብ ራስን መቻል፣ የምግብ ዋስትና እና የምግብ ሉዓላዊነት ናቸው:: በምግብ ራስን መቻል ሲባልም ሀገራት ከውጭ በሚገቡ ምርቶች ላይ ጥገኛ ሳይሆኑ የሕዝባቸውን ፍላጎት ለማሟላት የሚያስችል በቂ የማምረት አቅምን የሚያሳይ ነው:: ስለዚህ የግብርና ምርትን መጨመር፣ የውጭ ምርቶችን መቀነስ፣ የምግብ አቅርቦትን ማረጋገጥ እና ለውጭ አቅርቦት ተጋላጭነትን መቀነስ ላይ ያጠነጥናል::

የምግብ ዋስትና ሲባል ደግሞ ከዚህ ትንሽ ሰፋ ያለ ጽንሰ ሃሳብ መሆኑን የጠቀሱት ፕሮፌሰር ደገፋ፣ በቂ ምግብ የማግኘት ጉዳይ ላይ እንደሚያተኩር አስረድተዋል:: አቅርቦት ላይ ብቻ ሳይሆን የአገልግሎቱ ተደራሽነትን የሚያጠቃልል ነውም ብለዋል:: እርሳቸው እንደሚሉት፤ የምግብ ዋስትና ጉዳይ አራት ምሰሶዎች አሉት:: አንዱ የምግብ በበቂ ሁኔታ መኖር ነው:: ሁለተኛው ተደራሽነት ሲሆን፣ ሶስተኛው ደግሞ አጠቃቀም፣ አራተኛው የሶስቱ ቀጣይነት እና መረጋገጥ ጉዳይ ላይ የሚያተኩር መሆኑን ፕሮፌሰር ደገፋ አስረድተዋል::

የምግብ ሉዓላዊነት ሲባል ደግሞ ሀገሮች የራሳቸውን የግብርና እና የምግብ ፖሊሲ የመወሰን መብቶቻቸውን ማስጠበቅ መቻል ላይ የሚያተኮር ነው:: ስለዚህ ሀገራት በሥነ ምህዳር ጤናማ እና በዘላቂነት የሚያመርቱት ጤናማ ባህላዊ ምግቦችን የማግኘት መብቶቻቸው እና የየራሳቸውን የምግብ እና የግብርና ሥርዓት የመወሰን መብታቸውን የሚያመላክት መሆኑን አብራርተዋል::

ፕሮፌሰር ደገፋ፣ እኤአ በ2024 በዓለም ደረጃ ከ700 ሚሊዮን ሕዝብ በላይ የምግብ ዋስትናው የተረጋገጠ አለመሆኑን ጠቅሰዋል:: እነዚህም ሳይጠግቡ ወደ መኝታቸው የሚሄዱ ሲሆን፣ ከዚህ መካከል ወደ ሃያ በመቶው በአፍሪካ ከሳራ በታች የሚኖሩ ናቸው ሲሉ ገልጸዋል::

ኢትዮጵያ በ1966 እና በ1977 ዓ.ም በምግብ እጦት የምትታወቅበት ጊዜ መሆኑን ያስታወሱት ፕሮፌሰር ደገፋ፣ በሰላሙም ጊዜ ቢሆንም በሚሊዮን የሚቆጠር የኢትዮጵያ ሕዝብ ለምግብ እጥረት የተጋለጠ መሆኑን አስታውሰዋል:: በአሁኑ ወቅትም ከአራት ኢትዮጵያውን መካከል አንዱ የምግብ ዋስትናው የተረጋገጠ አለመሆኑን አመልክተዋል:: ከአስር ሚሊዮን ሕዝብ በላይ ኑሮው በልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራም ላይ የተመሰረተ እንደሆነም ገልጸዋል:: ወደ አምስት ሚሊዮን የሚጠጋው ሕዝብ ደግሞ በከፍተኛ እርዳታ እህል እየተዳደረ ያለ ነው ብለዋል::

ፕሮፌሰር ደገፋ፣ ለዚህ ዋና ዋና መንስዔ ናቸው ያሉት አራት ሲሆኑ፣ እነዚህም ተደጋጋሚ የሆነ ድርቅ፣ የአፈር መሸርሸርና የአየር ንብረት ለውጥ፣ የመሠረተ ልማት እና የግብዓት አለመሟላት እና የኢንቨስትመንት እጥረት እንደሆኑ አብራርተዋል::

> **የምግብ ሥርዓቱ የተንጠለጠለው ዝናብ ላይ ሲሆን፣ ይህ ደግሞ የሚወሰነው እንደየዝናቡ ሁኔታ ነው:: ሌላው የምግብ ዋስትና እንዳይረጋገጥ ተግዳሮት የሆነው የሕዝብ ቁጥር መጨመር ነው**

በኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና ያለመረጋገጡ መንስኤ ምንድን ነው? ለማሻሻልስ መደረግ ያለበት ምንድን ነው? የምግብ ዋስትና መረጋገጥ የማን ኃላፊነት ነው? በሚል ዙሪያ ምሁራዊ እይታቸውን እንዲያካፍሉ ከተጋበዙት መካከል አንዱ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የልማት ጥናት ኮሌጅ ፕሮፌሰር በላይ ስማኔ (ዶ/ር) ሲሆኑ፣ ሌላኛው ደግሞ የግብርና ኢኮኖሚስቱ ዳዊት ዓለሙ (ዶ/ር) ናቸው::

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የልማት ጥናት ኮሌጅ ፕሮፌሰር በላይ ስማኔ (ዶ/ር) ያለፉት ዓመታትንና የአሁኑን የኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና ሁኔታን በተመለከተ እንደሚናገሩት፤ ባለፉት ዓመታት ግብርናን እና የምግብ ዋስትናን ለማሻሻል ብዙ ጥረት ተደርጓል:: ከዚህ የተነሳ ምርትና ምርታማነት በተወሰነ ደረጃ አድጓል:: ለምሳሌ እኤአ በ1990 ወደ አስር ኩንታል የነበረው አማካይ ምርት በ2011 ላይ ወደ ሃያ ኩንታል መድረስ ችሏል:: በቅርቡ ደግሞ በ2022 እስከ 23 ኩንታል ደርሷል:: ስለዚህ ሙከራዎች መኖራቸውን ያመላክታል:: ይሁንና የኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና በሰፊው አልተረጋገጠም::

በአሁኑ ወቅት የምግብ ዋስትና ማጣትም መስፋፋትም ወደ 58 ነጥብ አንድ በመቶ የደረሰ ነው:: ይህ በቁጥር ሲሰላ ከሰብ ሰሃራ አፍሪካ ከአፍሪካም እጅግ በጣም አሳሳቢ ደረጃ ላይ የደረስን ነን:: ሌላው ማሳያ ደግሞ የመቀንጨር ሁኔታ አሁን የሚታየው እስከ 34 ነጥብ አራት በመቶ ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ ይገኛል:: ስለዚህ በእርሳቸው እምነት ኢትዮጵያ ውስጥ የምግብ ዋስትና አልተረጋገጠም::

የግብርና ኢኮኖሚስቱ ዳዊት ዓለሙ (ዶ/ር)፣ በበኩላቸው እንደሚሉት፤ የኢትዮጵያ የምግብ ዋስትና ሁኔታ ከዓመት ዓመት የተለያየ ነው:: የምግብ ሥርዓቱ የተንጠለጠለው ዝናብ ላይ ሲሆን፣ ይህ ደግሞ የሚወሰነው እንደየዝናቡ ሁኔታ ነው:: ሌላው የምግብ ዋስትና እንዳይረጋገጥ ተግዳሮት የሆነው የሕዝብ ቁጥር መጨመር ነው:: ምክንያቱም ቀደም ሲል ወደ 20 እና 25 ሚሊዮን አካባቢ የነበረ ሕዝብ በአሁኑ ወቅት እስከ 130 ሚሊዮን የተጠጋ ነው

እዚህ ላይ የመንግሥት ሚና ከፍተኛ መሆኑን ጠቅሰው፤ በተለይ መንግሥት የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ በሰፊው ከዘረጋቸው ፕሮግራሞች አንዱ ልማታዊ ሴፍትኔት ፕሮግራም ነው:: በዚህ ፕሮግራም የሚሳተፈው ቁጥር ደግሞ መቀነስ ሲገባው ከዓመት ዓመት እየጨመረ የመጣ ነው:: ለአብነት ያህል የአማራ ክልል ቢወሰድ በፊት ከነበረው ተጨማሪ 17 ወረዳዎች በዚህ ፕሮግራም የታቀፉ ናቸው:: ከዚህ የተነሳ የዕለት ጉርስ ፈላጊው በርክቶ ይታያል ማለት ነው:: ስለሆነም የምግብ ዋስትና ሁኔታው እየባሰ እና ፈታኝ እየሆነ ነው ሲሉ ከፕሮፌሰር በላይ ሃሳብ ጋር ይስማማሉ::

ታዲያ የዘርፉ ምሁራን ኢትዮጵያ በምግብ ራሷን ያለመቻሏ ምክንያት ምን ይሆን ለሚለው ፕሮፌሰር በላይ እንደሚሉት፤ የምግብ ዋስትና ለማረጋገጥ እንዳይቻል ያደረገው ምክንያት ውስብስብ ከመሆኑ የተነሳ እርስ በእርሱ እንኳ ለማስታረቅ የቸገረ ጉዳይ ነው:: ይህ ፈተና ኢትዮጵያንንም አፍሪካንንም የነካ ነው:: ከዚህ ውስጥ አንዱ የአየር ንብረት ለውጥ ነው:: እኤአ ከ1960 ጀምሮ ወደ አንድ ነጥብ አንድ ዲግሪ ሴልሺየስ ሙቀት ጨምሯል:: በሚቀጥሉት እስከ 2050 ድረስ በኢትዮጵያ ውስጥ እስከ ሶስት ዲግሪ ሲልሺየስ ሙቀት እንደሚጨምር ይጠበቃል:: በዚያው ልክ የዝናብ ሥርጭትም፣ የጎርፉና የድርቁም ሁኔታ በጣም ይጨምራል ተብሎ ይጠበቃል:: በእያንዳንዱ ዲግሪ ሴልሼየስ ጭማሪ እስከ አስር በመቶ ምርታማነት ይቀንሳል የሚል ጥናት አለ:: ስለሆነም አንዱ ትልቁ ችግር ይህ ነው ይላሉ::

ፕሮፌሰር በላይ አክለው ፣ ሁለተኛው ትልቁ ችግር ልክ እንደ ዳዊት (ዶ/ር)ሁሉ የሕዝብ ብዛት መጨመር ነው ይላሉ:: የሕዝብ ቁጥር መጨመር የተፈጥሮ ሀብት ላይ የማይሆን ጫና እያሳደረ ነው:: ለምሳሌ የኢትዮጵያ ሕዝብ አሁን ባለው የሕዝብ መጨመር ስሌት ሲሰላ በ2050 ደግሞ ወደ 215 ሚሊዮን ሕዝብ ይደርሳል ተብሎ ይጠበቃል:: ይህ በግብርና እይታ መብዛቱ ሳይሆን ሕዝቡ ምግብ፣ ማገዶ፣ ቤት ይፈልጋል:: ስለዚህ በአሁኑ ወቅት የሕዝብ ጥግግት በስኩዌር ኪሎ ሜትር 105 ሰው ነው:: በ2050 ደግሞ በስኩዌር ኪሎ ሜትር ወደ 193 ሰው ይደርሳል ይላሉ::

ሶስተኛው ምክንያት ብለው ፕሮፌሰር በላይ የጠቀሱት የማኅበራዊ አለመረጋጋትን ነው:: ግብርናን በአግባቡ ለመሥራትና የተመረተውንም ምርት ከቦታ ቦታ ለመውሰድ ማኅበራዊ አለመረጋጋት ከፍተኛ አስተዋጽኦ አለው:: ከዚህ በተጨማሪ የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓት እጥረትም ሆነ የመሬታችን መጎሳቆል ምርት እንዲቀንስብን አድርጓል ሲሉ ያስረዳሉ::

ለምሳሌ አብዛኛው አርሶ አደር ከጤፍ ምርት እየወጣ ወደ ባህርዛፍ ምርት እየገባ መሆኑንም ያስታውሳሉ:: ከዚህ የተነሳ ብዙ የመስኖ ቦታዎች ጨዋማ እየሆኑ ይገኛሉ::

ዳዊት (ዶ/ር) በበኩላቸው፤ ኢትዮጵያ በምግብ ራሷን ያለመቻሏ ምክንያት ያሉት አንደኛው እንደ ፕሮፌሰር በላይ ሁሉ ምርትና ምርታማነት ማነስ ነው ይላሉ፤ ምክንያቱ ደግሞ መሬትን በአግባቡ አለመያዝና ግብዓትንም ካለመጠቀም ጋር የተያያዘ መሆኑን ያስረዳሉ:: ከዚህ ጋር በተያያዘ የምርጥ ዘር አለመጠቀማችን ነው::

ምርጥ ዘር መጠቀም ከ20 እስከ 40 በመቶ ምርታማነትን እንደሚጨምርም አስታውሰዋል:: ሌላው የመስኖ አቅማችንን ባለመጠቀማችንና የመስኖ ልማቱ መዳከሙ ነው ብለው እንደሚያምኑ ይናገራሉ::

ፕሮፌሰር በላይ እንደሚሉት፤ የምግብ ዋስትናውን ለማሻሻል መደረግ ያለበት በጥናት በተደገፈ ፖሊስና ተቋማዊ አደረጃጀት ማበረታቻ ቢደረግ ጥሩ ነው:: ለምሳሌ ድሮ የነበረ ዓይነት የግብዓት ድጎማ ወሳኝ ነው:: ይህ ዓይነቱ አሠራር በብዙ የአውሮፓና የኢስያ ሀገራት ያለ ነው:: ሁለተኛው የግብርና መሠረተ ልማትን ማሳደግና ከግብርና ጋር የተያያዙ አግሮ ኢንዱስትሪዎችን ማስፋፋት መልካም ነው:: ሶስተኛው ምርምርና ልማትን በእውቀትና በክህሎት እንዲመራ ማድረግ እንዲሁም ኤክስቴንሽኑን ከፖለቲካው መነጠል ያስፈልጋል::

የተፈጥሮ ሀብት መጎሳቆልን ለማስቀረት በእያንዳንዱ አግሮ ኢኮሎጂና ሥርዓተ ምህዳር ተስማሚ የሆኑ የተፈጥሮ ሀብት እንክብካቤ ላይ ቢሰራ መልካም ነው ብለዋል:: ኢትዮጵያ ማዳበሪያና ምርጥ ዘርን በተመለከተ ራሷን እንድትችል ቢጣር የተሻለ ነው::

ሀገራችን ወደ 48 አካባቢ አግሮ ኢኮሎጂ አላት ቢባልም የግብርና ሚኒስቴሩ እውቅና የሰጠው ወደ 32 አግሮ ኢኮሎጂ ነው የሚሉት ደግሞ ዳዊት (ዶ/ር) ናቸው:: ከዚህ የተነሳ በየትኛውም አካባቢ ያለ ሁሉ በእኛ ሀገር መብቀል ይችላል ይላሉ:: ይሁንና ለምሳሌ የአትክልት ዘሮችን ሙሉ ለሙሉ በሚያስብል ሁኔታ ከውጭ እያስገባን ነው ሲሉ ጠቅሰው፤ ይሁንና ኢትዮጵያ ውስጥ መመረት የሚችሉ በመሆናቸው በእዚህ ላይ መሥራት ያስፈልጋል ብለዋል:: በተጨማሪም ሀገር በቀል እውቀትንም መቃኘቱ ተገቢ ነው ሲሉ ተናግረዋል:: የምግብ ዋስትና ፕሮግራሞችም ሲቀረጹ ሀገር በቀል እውቀቶችን አካትተው ቢሆን መልካም እንደሆነ አስረድተዋል::

በሀገር አቀፍ ደረጃና በቤተሰብ ደረጃ የምግብ ዋስትናን ማረጋገጥ ኃላፊነቱ የአንድ አካል ብቻ ሳይሆን ተዋንያኑ ብዙ ነው የሚሉት ፕሮፌሰር በላይ፣ ዋና ተዋናይ ግን መንግሥት ነው ይላሉ:: አግባብነት ያለውና ሊተገበር የሚችል ፖሊሲ ማውጣት ከመንግሥት የሚጠበቅ ነው:: ሁለተኛው ከምርምር ተቋማት ብዙ የሚጠበቅ መሆኑ ሊዘነጋ አይገባም:: ምርምሮችን ማፍለቅና ማሰራጨት ላይ በሰፊው መሳተፍ አለባቸው:: ሶስተኛው ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ኃላፊነት ያለባቸው ሲሆን፣ ሀገር በቀል እውቀትንም ከግምት ማስገባት ይጠበቅባቸዋል:: በግብርናው ላይ የተሰማሩ የግል ባለሀብቶች ትርፍን ለማሳደግ ብቻ ሳይሆን ቀጣይነት ባለው ልማት ላይ በማተኮር እነርሱም አርሶ አደሩም ተጠቃሚ እንዲሆን ሊሰሩ ይገባል::

ግብርናው ሀገር በቀል በሆነ ቴክኖሎጂና ሀገር በቀል ሳይንቲስቶች የሚመራ ባለመሆኑ ብዙ ነገር የተመሰቃቀለ እንደሚመስላቸው የጠቀሱት ፕሮፌሰሩ፣ እነዚህን ሀገር በቀል እውቀቶችን መመለስ እንደሚያስፈልግ ተናግረዋል::

መንግሥትና የግሉ ሴክተር ተናብበው መሥራት አለባቸው የሚሉት ደግሞ ዳዊት (ዶ/ር) ናቸው:: ሌላው የግብይት ሥርዓቱ መታየት ያለበት ጉዳይ ነው ሲሉ ጠቅሰው፤ አሁን ድረስ ገበያ አጥቶ የሚሰቃይ አርሶ አደር እንዳለ ሁሉ፤ ምግብ አጥቶ የሚሰቃይ ሕዝብ አሉ በማለት ገልጸዋል:: ከዚህ አንጻር የገበያ ሥርዓቱ መታየት እንዳለበት አስረድተዋል::

የዘርፉ ምሁራን ኢትዮጵያ አሁን ከምታመርተው ጭማሪ ማምረት እንዳለባት ጠቅሰው፤ ሀገር በቀል እውቀትም ከግምት መግባት እንዳለበት አመልክተዋል:: የምርጥ ዘር የግብይት ሥርዓት ቢጠናከርና የግብርና ምርት ማሳደጊያ ግብዓትም በጊዜው ቢደርስ ውጤቱ ያማረ እንደሚሆን አብራርተዋል:: ምርምርና ልማትን በእውቀትና በክህሎት እንዲመራ ማድረግም ተገቢነቱ ላይ አስምረዋል::

ማህበራዊ

# ሴቶች

# ከድባቴ ጀርባ ያሉ ውብ ልቦች ...

ሰሚራ በርሀ

ዲዛይነር ለመሆን የተገኘችበት ቤተሰብ መነሻ እንደሆነ ታነሳለች ። « ገባይል ፎር አል » የተሰኘ የፋሽን ዲዛይን መስራች፣ ዲዛይነርና ዳይሬክተር ናት። የፋሽን ዲዛይን ልብሶችን ከመሥራት ባሻገር የሀገራዊነት ስሜትን የሚያንጸባርቁ ውበትን ወጣትነትን የሚገልጹ ሃሳቦቿን የምታሳርፍባቸውን ሥራዎቿን ወደ ገበያው ይዛ ቀርባለች።

ዲዛይነር መሆን የልጅነት ፍላጎቷ በመሆኑ አሁን ያለችበት ደረጃ ለመድረስ ቀላል የማይባሉ መንገዶችን አልፋ አሁን የደረሰችበት ላይ ትገኛለች። በዛሬው የሴቶች ገጽ ላይ ሙያዋን በመጠቀም መልዕክት ማስተላለፍ የሚችሉ ልብሶች ከምትሰራ እና የራሷን የፋሽን ዲዛይን ብራንድ ገንብታ በሥራ ላይ ከምትገኝ ዲዛይነር ጋር ቆይታ አድርገናል። መልካም ንባብ ...

ገባይል አሰግድ ትባላለች። የስሟ ትርጓሜም ሕዝባዊት የብዙ የሆነች የሚል ነው። ሥራዎቿንም በስሟ ስትሰይመው አላማው ብዙዎች ጋር መድረስ የሚችሉ ልብሶችን ሰርቶ ለማቅረብ ነው። « በባህሪዬ ለሀበሻ ልብሶች ቅርብ ነኝ ፤ ነገር ግን የሀበሻ ልብሶች የበዓላት ወቅትን ብቻ ጠብቀው ነው የሚለበሱት የሚለውን ሃሳብ አልስማማበትም » የምትለው ገባይል የምትሰራቻው ልብሶች ሰዎች የሀበሻ ልብስን ለሥራ፤ ለመዝናኛ ቀናት እና በፈለጉት ሁነት እና ቦታ በነፃነት እንዲጠቀሙበት ትፈልጋለች።

ገባይል ወደ ፋሽን የተሳበችበትን አጋጣሚ ስትገልጽ «እናቴ በቤት ውስጥ የተለያዩ ልብሶችን ትሰራ ነበር። አያቴም 10 ልጆች ስለነበሯት በራሷ መስፊያ ማሽን የተለያዩ ልብሶችን ትሰራላቸው ነበር።» በተጨማሪም ገባይል የአንደኛ ደረጃ ትምህርቷን በተከታተለችበት የናዝሬት አንደኛ ደረጃ የሴቶች ትምህርት ቤት ራሱን የቻለ የእጅ ሥራ ትምህርት ነበር። በዚህ ሰዓት ገባይል ሥዕል የእጅ ሥራ ክህሎትን በይበልጥ እንድትለምደው እና ፍላጎቱ እንዲያድርባት ሆነ። ታዲያ በልጅነት እድሜዋ ለመጫወቻነት የሚገዙላትን አሻንጉሊቶች ቤት ውስጥ ያገኘችውን ጨርቅ እየቀደደች ፣ እየለካችና እየቆረጠች ለአሻንጉሊቶቿ ልብሶችን ትሰራለች።

የፋሽን ዲዛይን ፍላጎት ያደረባት ገባይል ይበልጥ እንድታውቀው የፋሽን ዲዛይን ትምህርት ቤት ገብታ መማርን ፈለገች፤ ነገር ግን ትምህርቷን ጭራሽ እንዳትተወው ስጋት ያደረባቸው እናት በዚህ እድሜ ወደ ፋሽን ማዘንበሏን አልወደዱትም ነበር። ገባይል የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን እንዳጠናቀቀች በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የመካኒካል ምህንድስና ትምህርትን መማር ጀመረች። የምትማረው ትምህርት ትኩረት የሚጠይቅ እና የፋታ ጊዜ የማይሰጥ ቢሆንም በዩኒቨርሲቲ ቆይታዋም የራሷን ልብሶች በምትፈልገው መንገድ ዲዛይን በማድረግ የፋሽን ዲዛይን ክህሎቷን በምትለብሳቸው ልብሶች ላይ ታንጸባርቅ ነበር።

የመካኒካል ምህንድስና አራተኛ ዓመት ተማሪ ሳለች ለፋሽን ዲዛይን ያላትን ፍላጎት የተረዳው ወንድሟ የፋሽን ዲዛይን ትምህርትን እንድትማር አገዛት እሷም ቀን ቀን በረዳት መካኒክነት ማታ ደግሞ ፋሽን ዲዛይን መማሯን ቀጠለች። የፋሽን ዲዛይን የአንድ ዓመት ስልጠናዋን ስታጠናቅቅ በረዳት መካኒክነት ለስድስት ወር ያክል ጊዜ ሰራች። የመካኒካል ምህንድስና ትምህርት ቀላል የሚባል አይደለም የምትለው ገባይል ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ትምህርቷን ስታጠናቅቅ በትምህርት ክፍሉ ከተመረቁ ስምንት ሴቶች ውስጥ አንዷ ነበረች።

«የፋሽን ትምህርት ቤት እንደገባሁ አስብ የነበረው ቶሎ ዲዛይነር መሆን ነበር። ነገር ግን ሥዕል መሳል ጨርቅ መቁረጥ እንዲሁም መስፋት ዲዛይነር አያስብልም የእነዚህ ሁሉ ክህሎቶች ድምር ዲዛይነር የሚለውን እንደሚፈጥር ተረድቻለሁ። » በማለት የነበራትን የትምህርት ቆይታ ታስታውሳለች። ትምህርቷን እንደጨረሰች ታላቅ ወንድሟ በገዛላት ማሽን ይበልጥ የራሷን ሥራዎች እንድትሰራ እና ችሎታዋን እንድታሳድግ ረዳት። ከመመረቋ በፊትም በቅርቧ ላሉ ጓደኞች እና ወዳጆቿ የተለያዩ ልብሶችን በመሥራት ቢዝነሷን ጀመረች።

ገባይል የምህንድና ትምህርቷን ካጠናቀቀች በኋላ የፋሽን ዲዛይን ትምህርት ቤት ከተዋወቀቻት ጓደኛዋ ጋር ሃሳባቸውን እና የወሰዱትን ትምህርት እንዴት ወደ ገበያ እንቀይረው በሚል ተማከሩ ፤ ከቤተሰቦቻቸው





ባገኙት መነሻ ገንዘብም የራሳቸውን ሱቅ መለያ ስም አልያም ብራንድ አውጥተው ቀጥታ ወደ ሥራ ገቡ። ይህም ገባይል የዩኒቨርሲቲ ትምህርቷን በጨረሰች ማግስት ነበር። «የተለያዩ የልብስ ትእዛዞችን በራሳችን እየተቀበልን እንሰራ ነበር። የምናውቅ የመሰሉን ነገር ግን ብዙ የማናውቃቸውን በንግድ ሥራ የሚያጋጥሙ ሁነቶችን አስተናግደናል ተምረንበታል።» የምትለው ገባይል ደንበኞችን እንዴት ማስተናገድ እንዳለባቸው ፣ የታዘዟቸውን ምርቶች ጊዜውን ጠብቆ በጥራት ማድረስ፣ ገበያው ላይ ለመቆየት ምን ማድረግ እንዳለባቸው ፣ ዋጋ ማውጣት ለተከራዩበት ሱቅ ከፍተኛ ክፍያ መጠየቅ እና ጓደኝነትና ቢዝነስን አብሮ ማስኬድ ከተፈተኑባቸው ጉዳዮች ውስጥ መሆኑን ታነሳለች።

በጣም ጥሩ የሚባሉ የሕይወት ልምዶች ከባድ የሚባሉት ጊዜያት ናቸው የምትለው ወጣቷ ዲዛይነር ከጓደኛዋ ጋር በነበራት የሥራ ቆይታ ብዙ መማሯን ትናገራለች። «ከቤተሰብ ተበድረን ስለነበር ሥራውን የጀመርነው ለተከራየንበት ሱቅ የምንከፍለውን ክፍያ በፍጹም ከቤተሰብ አልጠየቅንም ባናተርፍም ግን የመጀመሪያውን ፈተና ተወጥተነዋል ብዬ አስባለሁ።» ትላለች። ሥራውን ለመጀመር የመረጡት የሥራ ቦታ ከፍተኛ ክፍያ መጠየቃቸው ፣ የራሳቸውን ደንበኞች ሳይገነቡ መጀመራቸው እንደ ፈተና የሚነሱ መሆናቸውን ጠቅሳለች።

በዚህ ሥራ ውስጥ አንድ ዓመት ያክል ጊዜ ከሰሩ በኋላ ቢዝነሱ አንድ ዘርፍ ላይ ያተኮረ ቢሆንም የሁለት ሰዎች እይታ የሚንጸባረቅበት በመሆኑ በሥራቸው መሀል የሌሎች ጉዳዮች ግፊትም ተጨምሮበት በሃሳብ አለመስማማት እንደነበር ገባይል ታስታውሳለች። ሥራቸው መቀጠል ባለመቻሉ ያሏትን ደንበኞች እና ሙያዋን ይዛ ከቤቷ መሥራት ጀመረች። « አሁን ባለንበት ኢኮኖሚ አብሮ መሥራትን እጅግ በጣም እደግፋለሁ፤ መተጋገዝ ይኖራል ነገር ግን አብሮ መሥራት ሕጋዊ መንገድን የተከተለ በሰነድ ማስረጃ የተደገፈ መሆን አለበት። » ስትል ትገልጻለች።

በተጨማሪም በጓደኝነት ውስጥ የተጀመረ ማንኛውም ሥራ የታለመለትን ውጤት እንዲያመጣ ሥራው ከጓደኝነት መብለጥ አለበት የሚል ሃሳብ አላት። ይህም በጉርብትናው አለመግባባት ቢፈጠር እንኳን ሥራው ግን እንዲቀጥል ያስችላል ስትል ትገልጻለች።

«እንደተመረቅኩ ሥራውን ስጀምር ቤተሰቦቼ በዙርያዬ ያለ ሰው ሊመክረኝ ወይም ይከብድሻል ተብዬ ነበር። ነገር ግን ሁሉንም ነገር ከሰው አንማረውም፤ ራሳችን ሞክረን ወይ ወድቀን እስካልተማርነው ድረስ አምነን አንቀበለውም። በሥራ ውስጥ ደግሞ ውድቀት ያለ ነገር ነው።» የምትለው ገባይል በዙርያዋ መልካም የሚባሉ ድጋፎችን በማግኘቷ በቤተሰቦቿ ዘንድ ይበልጥ እንድትሰራ ድጋፍን ማግኘቷን በመንፈሳዊ ሕይወቷ ያላት ጥንካሬም እንደጠቀማት ትናገራለች።

ገባይል የፋሽን ዲዛይን ሥራ ከቤቷ ለመጀመር ስታስብ ሌላ ከባድ ነገር በሕይወቷ አስተናገደች ፤ እሱም የአባቷ ማረፍ ነበር። « በወጣትነት እድሜያችን የሚያስደስተን ነገር በጣም ውስን ነው ቤተሰብ ፣ ጓደኛ ጥቂት ነው በመሆኑም አባቴን ማጣቴ እና የደረሰብኝ ኪሳራ እንደ ወጣት እጅግ በጣም ከብዶኝ ነበር።» ትላለች።

በዚያን ወቅት አፍሪካን ሞዛይክ የተሰኘ በየዓመቱ ለፋሽን ዲዛይነሮች የሚሰጥ የስልጠና ፕሮግራም ይፋ ሲሆን ስልጠናው ብዙ ዲዛይነሮች የሚፈልጉት ቢሆንም ገባይል በሰዓቱ ይህን ስልጠና ለመውሰድም ሆነ በሙሉ አቅም ወደ ሥራ ለመግባት የስሜት ዝግጁነት አልነበራትም። « ለወላጆቼ ብቸኛ ሴት ልጅ ስሆን ከአባቴ ጋር በጣም ጥብቅ ግንኙነት ነበረኝ፤ በመሆኑም የአባቴን ህልፈት መቀበል አቅቶኝ ነበር ፤ ስልጠናውንም ልወስድ የቻልኩት በእናቴ ግፊት ነው።» ስትል ሁኔታውን ትገልጻለች።

የአፍሪካን ሞዛይክ ስልጠና የወሰዱ ዲዛይነሮች የራሳቸውን ሃሳብ የሚያንጸባርቁበት የሃሳብ ንድፍና የእጅ ሥራዎቻቸውን ውጤት እንዲያቀርቡ በስልጠናው ማብቂያ ላይ ይደረጋል። ገባይል የአባቷን ህልፈት ተከትሎ የጭንቀት ስሜትን ለተወሰኑ ጊዜያት አስተናግዳ ያለፈች ሲሆን በዙርያዋም ከዚህ ስሜት መውጣት ያልቻሉ አለፍ ሲልም ራሳቸውን እስከ ማጥፋት ድረስ የደረሱ ሰዎች ነበሩ። « ስለ አዕምሮ ጤና የነበረኝ አመለካከት ልክ እንደ ሌላው ሰው ከሃይማኖታዊ ነገር ጋር የተገናኘ ነበር። አዕምሮ እንደ ማንኛውም ሰውነታችን ክፍል ታክሞ መዳን የሚችል ነው። ሰዎች እንደመሆናችን በተለያየ የሕይወት መንገድ ውስጥ እንሰበራለን፤ ነገር ግን አንገጣጠምም ማለት አይደለም። የአዕምሮ ጤናን በሕክምና ከሰዎች ጋር በማውራት እና ከራሳችን ሌላ እድል በመስጠት ማሸነፍ እንችላለን።» በማለት ከደረሰባት ችግር የወጣችበትን ዘዴ ትናገራለች።

ገባይልም ይህን የጭንቀት ወቅት ከሥራ ጋር የተገናኙ ስልጠናዎችን በመውሰድ ሥራዋ ላይ በማተኮር እና በሥራ በመወጠር ከዚህ የጭንቀት ስሜት መውጣት ችላለች። ሰዎች ሁልግዜም እንደ አዲስ የሚያስተናግዱት የማይለምዱት ስሜት ተብሎ የሚወሰደው በሕይወታቸው ውስጥ ቦታ የሚሰጡት የሚወዱትን ሰው ማጣት ነው። ገባይል ሀዘንን የምናስተናግድበት መንገድ ማየት ይገባል ትላለች «ሀዘን አምስት ሂደቶች አሉት፤ የመጀመሪያው ድንጋጤ ነው። ከዚያም ንዴት ሲሆን ሶስተኛው ደግሞ እውነታውን መካድ አልያም መቀበል አለመፈለግ ፤ ሌሎች ሰዎች ላይ መጠቆም ፤ አልያም ተጠያቂ ማድረግ ሲሆን ድብርት ውስጥ መግባት ከዚያም አለፍ ሲልም ሁኔታውን ወደ መቀበል ይደርሳል። የብዙ ሰዎች ችግር ግን ከእነዚህ ሂደቶች ላይ በአንዱ በጣም በመቆየት ራሳቸውን ወደ መጉዳት ጥሩ የማይባል የባህሪ ለውጥ ሲያመጡ እናይባቸዋለን።» በማለት ያለፈችበት የድባቴ እና የጭንቀት ወቅት ታስታውሰዋለች።

ገባይል ስለ አዕምሮ ጤና ጥናት ካደረገች በኋላም «ከድባቴ ጀርባ ያሉ ውብ ልቦች የሚል መጠሪያ ያለው» ሥራዎቿን ይዛ ቀረበች። በአፍሪካን ሞዛይክ ላይ ይዛ የቀረበችው ስብስብም በጀርመን ሀገር በርሊን የፋሽን ሳምንት «ኒዮ የፋሽን መድረክ» ላይ ኢትዮጵያን ወክላ ሥራዎቿን ይዛ የመቅረብ እድሉን አገኘች። በዚያም የአዕምሮ ጤናን በፋሽን ዲዛይን ለመግለጽ የሞከረችበት መንገድ አድናቆትን አግኝቶ የበርሊን እና እንግሊዝ ሀገር ዓለም አቀፍ ጋዜጦች ላይ ሽፋን ተሰጠው።

ገባይል ይህን እድል ያገኘችው ባላት ነገር የራሷን ሥራ በጀመረችበት ወቅት ነበር። «በዚህ ሥራ የተማርኩት ወጣት ስንሆን ከፍላጎታችን እና መሬት ላይ ካለው እውነታ ጋር የምናደርገው ግብግብ ያልተገባ ጊዜ እንድናጠፋ ያደርገናል። ያለንበትን ሁኔታ ስንቀበል ግን እድሎችን መድረኮችን እናገኛለን።» ስትል ሁኔታዎችን መረዳት ያለውን ጠቀሜታ ታስረዳለች።

ገባይል የራሷን ሥራ ለመሥራት ወስና በመኖሪያ ቤቷ እናቷ ትሰራ በነበረበት ሱቅ ውስጥ ሥራዎቿን እንደ አዲስ ጀመረች። ሥራዎቿን በተለያዩ የማህበራዊ ገጾች ላይ በማስተዋወቅ በየጊዜው ብራንዷን ሃሳቧን የምታንጸባርቅበት ልብሶችን መሥራት እና ለገበያ ማውጣት የተለያዩ የፋሽን ትርኢቶች ላይ ሥራዎቿን ይዛ ብቅ ትላለች።

«ገባይል ፎር አል» ብላ የሰየመችውን ሥራዎቿን ስትገልጻቸው ቀለል ያለ ነገር ግን ውበትና ግርማ ሞገስን የተላበሱ በማለት ትገልጻቸዋለች። የድሮ ፋሽኖች ይስቡኛል የምትለው ገባይል አያቷ በነበሩበት ዘመን ይለብሷቸው የነበሩ በብር ፣ በነሃስ እንዲሁም ጥሩ ኢኮኖሚ ያላቸው እንስቶች ደግሞ በወርቅ ጭምር የተጌጡ ልብሶችን ይለብሱ እንደነበር ታስታውሳለች።

እሷም ከዚህ በመነሳት በሸማኔ በተሠራው የፈትል ጨርቅ ላይ በተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች የሚገኙ እንስቶች በአንገታቸው፣ በእጃቸው ላይ የሚያደርጓቸውን ማጌጫዎች በማከል ልብሱ የተለየ ውበት እንዲሰጥ አድርጋ ትሰራለች። ጌጣጌጦቹን ከአክሱም ፣ ከላሊበላ የምታገኛቸው ሲሆን በምትፈልገው መንገድ ዲዛይን በማድረግ ጌጣጌጦቹን በልብሶቹ ላይ ትጠቀምበታለች። መነሻው ከአያቷ የሆነው የዚህ ዲዛይን ስያሜም «እማዬ የወረደች ቀሚስ።» የሚል ነበር። «ከ80 በመቶ በላይ የሚሆነውን ግብዓት እዚሁ በሀገራችን የተመረተ እንዲሆን ነው የምንፈልገው አብዛኛዎቹ ልብሶችም ሽመና ናቸው።» ትላለች።

ገባይል የምትሰራቻውን ልብሶች ቀለል ያሉ እና ውበትን የሚያጎናጽፉ በማለት ትገልጻቸዋለች። እነዚህንም ልብሶች ለመሥራት በዋናነት የሀገር ባህል ልብሶች የሚሰሩባቸውን ግብዓቶች ትጠቀማለች። ምንም እንኳን የምትጠቀመው የሀበሻ ፈትል ጨርቅን ቢሆንም አሠራሩ ከተለመደው የሀበሻ ልብስ የተለየ በመሆኑ ሰዎች ጋር ለማስተዋወቅ በምትገኝባቸው መድረኮች እና ዝግጅቶች ላይ እራሷ ለብሳው ትሄዳለች። በዚያም ሰዎች እንድትሰራላቸው ይጠይቋታል፤ በዚህ መንገድ ሰዎች ጋር እንዲደርስ የተለያዩ ሞዴሎችን በመጠቀም በማህበራዊ ገጽ ሥራዎቿን ታስተዋውቃለች። ለሌላ ሰው የሰራችውን አይተው ወደ እርሷ የሚመጡ ደንበኞችም እንዳሉ ታነሳለች።

በራሳቸው ሥራ ውስጥ ላሉ እና ማንኛውንም የራሳቸውን ሥራ መጀመር ለሚፈልጉ ወጣቶችም ገባይል ሁለት ሃሳቦች አሏት «የራስ ሥራ ውጤቱ በፍጥነት ላይታይበት ይችላል። ስለዚህ በጣም ትዕግስተኛ መሆን ያስፈልጋል። ሌላኛው ደግሞ ሁሌም ራስን ከሰው ጋር ማወዳደር እጅግ በጣም የሚገል በመሆኑ ራሳችንን ካለፈው የእኛ ማንነት ጋር እያወዳደርን ሁሌም አዲስ ነገር ለመማርና ራስን ለማሻሻል በመሞከር ውስጥ ማለፍ ይገባል።» ትላለች።

ገባይል በአሁኑ ወቅት ሶስት ሠራተኞችን ይዛ እየሠራች ትገኛለች። የወደፊት እቅዷ ምርቶቿን በተለያዩ ሰዎች የልኬት መጠን ሰርታ በማዘጋጀት ሰዎች ወደ ሱቋ መጥተው ጊዜ ሳያጠፉ የወደዱትን ልብስ ለክተው ይዘው የሚሄዱበትን መንገድ መፍጠር ፣ ቅርንጫፎችን መክፈት እና ሥራዎቿ ከኢትዮጵያ ውጭ ባሉ ዓለም አቀፍ ገበያዎች ላይ እንዲገኙ ማድረግ የወደፊት ህልሟ ነው።

# ማረፊያ

## አዲስ ዘመን ድሮ

በዛሬው አዲስ ዘመን ድሮ ዓምዳችን ከቀደምት ጋዜጦች ለትውስታ ያህል ከሁለት የተለያዩ ሰፊ ዓምዶች ግርምትን የሚፈጥሩ ታሪኮችን መርጠናል። ገንዘብና ዝና ለማግኘት መስተዋት እበላለሁ፣ የዳቦ ነጋዴዎች እየቆመሩብን ነው.. የመረጥናቸው ሃሳቦች ሲሆኑ ከሳምንቱ አጋጣሚዎች ሁለቱን ለቅምሻ ያህል አክለን እንደሚከተለው ልናስታውሳችሁ ወደናል።

### "...ገንዘብና ዝና ለማግኘት መስተዋት እበላለሁ"

በዓለማችን ለትውልድ የሚተርፍ አኩሪ ተግባር የፈጸሙ ልዩ ተሰጥዖና ተደናቂነትን ያተረፉ ከሞቱ በኋላ እንኳን ስማቸው ዛሬም ገኖ የምንሰማው ተሰምቶአል:: እናም ባልተጠና መልኩ ወደ አደባባይ ብቅ የሚሉ እነዚህን የመሳሰሉ ሰዎች በጀብደኝነት የሚከተሏቸው ወጣቶች እንደማይጠፉ ሊታወቅ ይገባል::

.............

በሃገራችን እራሳቸውን ከሞትና ከአደጋ ጋር አፋጠው መጨረሻቸው ያላማረ ሆኖ የተገኙ ሰዎች ቁጥር ቀላል አይደለም:: ለዚህም በአንድ ወቅት በየነ የተባለ ግለሰብ ብረታ ብረትን እየቆረጣጠመ "ታዋቂነትን" ለማትረፍ ሲል እድሜው አጥሯል:: በሌላ ወቅት በአፉ እሳት ሲጎርስ፣ ምላጭ ሲውጥ የነበረ ሰውም እንዲሁ ሕይወቱ አልፏል::

..........

ሰሞኑን በአደባባይ ብቅ ብሎ "ድንቅ" ተግባሩን በማሳየት ላይ የሚገኘውን የኢሉባቦር ተወላጅ የሆነው ሀሰን መሐመድ ሀሰን የፍሎረሰንት መብራት፣ የመስተዋትና የአምፖል ስብርባሪዎችን ከያዘው ፌስታል ውስጥ እያወጣ በጥርሶቹ እየከሸከሸና በውሃ እያወራረደ ሲበላ አይተናል::

በቤተሰብ ምክንያት ሠላም በማጣቱ ወደ ዓረብ ሀገር ከእህት ወንድሞቹ ጋር መሰደዱን እንዲሁም የመኖሪያ ፈቃድ ባለማግኘቱ ሳይሳካለት ከጥቂት ወራት በፊት ወደ ሀገሩ ለመመለስ መገደዱን ይናገራል:: ይሁንና እናቱ በማረፋቸውና ሀብታም ነጋዴ ናቸው የሚላቸው አባቱ ተገቢውን ድጋፍ ስላላደረጉለት ቤተሰቡን ተቀይሞ ወደ አዲስ አበባ መምጣቱን ይናገራል:: ከሀገር ተመልሶ ወደ ውጪ ለመውጣት አማራጭ አድርጎ የወሰደው መስታወት መብላትን ነው::

........

ከዚያስ....ከሀሰን ጋር ያደረግነው ቃለ ምልልስ ይህን ይመስላል፡-

በአሁኑ ወቅት መስተዋት ለመብላት ምን አነሳሳህ?

"መስተዋት መብላት መቻሌን ለሕዝብ ለማሳየት ነው"

እኮ ለምን?

"በቃ...ኑሮን ማሸነፍ እፈልጋለሁ፤ ገንዘብ ዝና ማግኘት ይኖርብኛል::"

ታዲያ ሌሎች ዘዴዎች ለመሞከር ለምን አላሰብክም... ለምሳሌ በሩጫ በእግር ኳስ ተጫዋችነት፤ ሕዝብንና እራስህን በሚጠቅም በልዩ ልዩ የፈጠራ ሥራ ታዋቂ መሆን ይቻላል?

"ለነገሩ በልጅነቴ ኳስ ጨዋታ እሞክር ነበር፤ የሚያበረታታኝ ጠፋ እንጂ በዚያ ዝነኛ መሆን እችል ነበር:: አሁን ግን ለጊዜው ያገኘሁት መፍትሔ መስተዋት መብላት ነው::"

..........

የወደፊት ዓላማህ ምንድነው?

"የኮብራ መስተዋት ለመብላት ነው:: ጠንካራውን የኮብራ መኪና መስተዋት በዚህም ዝና፣ ገንዘብ ለማግኘት እሻለሁ::"

**( አዲስ ዘመን ታኅሣሥ 6 ቀን 1986 ዓ.ም)**

### የዳቦ ነጋዴዎች እየቆመሩብን ነው

ዳቦ-ድሮ ቀረ ከሚባሉ ነገሮች አንዱ ነው:: ዳቦ መጠኑ በሚያሳዝን ሁኔታ እየቀነሰ ጥራቱም እያሽቆለቆለ፣ ዋጋው ደግሞ እየተተኮሰ ይታያል::

..............

የድሮ ዳቦ መልኩ ብቻ ይበቃ ነበር ብል የምን ማገነን ነው እንደማትሉኝ ተስፋ አደርጋለሁ::

...........

ወዝ የሌለው ዳቦ በየቦታው ሞልቷል:: ዳቦ ከተባለ ማለቴ ነው:: እንቡጥ አይገኝበትም:: ያሳስራል፣ ያስቀጣል፣ ተብለው ይሆን ውሃ አጥቶ እንደደረቀ ቅጠል የሚያቆረፍዱት; በእዚህ ላይ መጠኑ በጣም እጅግ ያስገርማል:: ኪኒን እያከለ መጥቷል:: በእዚህ ላይ ተፈርፍሮ የሚያልቀውና ቤት የሚያበላሸው አይነሳም:: የሀምሳ ሳንቲም ዳቦ ስትገዛ የሁለት ብር መጥረጊያ መግዛትህን እንዳትረሳ እየተባለ የሚነገረውም ለዚሁ አይደል፡ የሱሙኒ ዶሮ የብር ገመድ ይዛ ጠፋች አይነት መሆኑ ነው::

......

ዛሬ ሕጻናት ሁለት ዳቦ በልተው አይጠግቡም:: እረ ይጨመርልን በሚል እያጉተመተሙ ነው ወደ ትምህርት ቤት የሚጓዙት:: ገና አንድ ክፍለ ጊዜ ሳይጨርሱ ሆዳቸው ምግብ ይጠይቃቸዋል:: አዋቂዎች አፋቸው ባዶ ባዶ እንዳይል ካልሆነ በስተቀር የዘመኑ ዳቦ አላረካቸውም:: ግማሹ ለአፈር የተቀረው ለከንፈር በመሆኑ ከሆድ አይደርስም::

........

የምንበላው ሳይሆን የምንስመው ዳቦ መጥቷል::

.....

የዳቦ ነጋዴዎች እስከመቼ ነው የሚቆምሩብን፡ ነዳጅ ጨመረ ሲባል በዚያው ልክ ዋጋ ይጨምሩብናል:: በ20 ሳንቲም ይሸጥ የነበረው ዛሬ እየቀረ ነው:: አንዳንዶቹ የ20 ሳንቲሙን 50 ይቀበሉበታል:: ግፍ የፈሩ ደግሞ የ50 ሳንቲሙን 60 ይቀበሉበታል::

.........

የዳቦ ነጋዴዎች በእኛ ስቃይ እንዴት ይከብራሉ:: ባንገዛቸውስ; ሌላ መላ መፈለግ አቅቶን ነው፣ እንደኔ እምነት ግን በአንድ ሰሞን ዘመቻ ዳቦ ቤቶችን ልክ ማግባት የሚቻል ይመስለኛል:: ዘንድሮስ እየቆመሩብን አይኖሩም የእስካሁኑ ይበቃል ባዮች በዝተዋል:: እባካቹ ጉዳዩ የሚመለከታችሁ ሁሉ የዳቦ ቤቶችን አሠራር የሚያስተካክል አፋጣኝ እርምጃ ውሰዱ?

**(አዲስ ዘመን ጥቅምት 17 ቀን 1989 ዓ.ም)**

### የሳምንቱ አጋጣሚዎች

ውስኪ በመወደዱ ምክንያት ብዙ ሰዎች አረቄ እየተለማመዱ ናቸው። ብዙዎች ውስኪ በመጥፋቱ ተናደዋል። እኔ ግን ሜታ ቢራን እወድ ስለነበረ በአካባቢዬ በመጥፋቱ የጎንደርን ጠጅ በግድ እየተለማመድኩ በዚህ ሳምንት አራት ብርሌ ጠጥቻለሁ።

እንዳለ ቶለሳ

ከብርድ ልብስ ተራ

ከባልንጀራዬ ጋር መጠጥ ጠጥተን በጣም ሰክረን ነበር። ታዲያ ከማስታውሰው ጨዋታ አንዱ ባልንጀራዬ ወደ ውጪ ሊወጣ ሲል ስለተንገዳገደ "አንተ ጠርሙስና ብርጭቆውን እንዳትሰብር" ብለው "ዶሮ እንቁላልዋን አትሰብርም"አለኝ።

ማናዬ

ከበዴሳ

**(አዲስ ዘመን ታኅሣሥ 8 ቀን 1988 ዓ.ም)**

# ዓለም አቀፍ

## ዛምቢያ የፀረ ሙስና ተቋሟ በሙስና ተዘፍቋል በሚል አመራሮቹን ከሥራ አገደች

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ደቡብ አፍሪካዊቷ ሀገር ዛምቢያ ሙስና ከተንሰራፋባቸው የአፍሪካ ሀገራት መካከል አንዷ ስትሆን በሥልጣን ላይ ያሉት የወቅቱ ፕሬዚዳንት ሀኪንዴ ሂቺለማ በሙስና ላይ ጥብቅ እርምጃ እንደሚወስዱ በተደጋጋሚ ሲናገሩ ይሰማሉ፡፡

የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት ሙስናን እንዲከላከሉ የተሾሙ የፀረ ሙስና ቦርድ አባላትን ከሥራ አግደዋል:: የፀረ ሙስና ቦርድ አባላቱ በሙሰኞች ላይ የተጀመሩ ምርመራዎችን ጉቦ እየተቀበሉ አቋርጠዋል ተብሏል፡፡

ፕሬዚዳንቱ ከሦስት ዓመት በፊት ወደ ሥልጣን እንደመጡም በቀድሞው የሀገሪቱ መንግሥት አስተዳደር ወቅት በሙስና ተግባር የተሳተፉ አመራሮች ላይ ጥብቅ ምርመራ እንዲደረግ እና ተጠያቂነት እንዲሰፍን በሚል አዲስ የፀረ ሙስና ቦርድ አቋቁመው ነበር፡፡

ይሁንና ሙስናን እንዲታገል የተቋቋመው ይህ ተቋም ራሱ በሙስና ተዘፍቆ ተገኝቷል በሚል የፀረ ሙስና ቦርዱ እንዲፈርስ ተደርጓል።

የዛምቢያ ፀረ ሙስና ቦርድ አራት ከፍተኛ አመራሮች ያሉት ሲሆን ቦርዱ በሙስና ተጠርጥረው ምርመራ እየተደረገባቸው የነበሩ ሰዎችን ሙስና እየተቀበሉ ምርመራውን እንዲቋረጥ አድርገዋል፡፡

በተለይም በቦርዱ ውስጥ ይሠራ የነበረ አንድ ባለሙያ በሙስና ተጠርጥረው ምርምራ ሲደረግባቸው የነበሩ የቀድሞ ፖለቲከኞች እጅ መንሻ እየሰጡ ምርመራቸው እንደተቋረጠላቸው ይፋ አድርጓል፡፡

ይህን ተከትሎ ጉዳዩ በመላው ዛምቢያ ዋነኛ የወቅቱ መነጋገሪያ የሆነ ሲሆን የፀረ ሙስና ቦርድ አመራሮች አስቀድመው ራሳቸውን ከኃላፊነት በማግለል ላይ መሆናቸው ተገልጿል፡፡

የሀገሪቱ ፕሬዚዳንት ጽሕፈት ቤት ዘግይቶ ባወጣው መግለጫ የፀረ ሙስና ቦርድ አመራሮች ራሳቸው በሙስና በመዘፈቃቸው ምክንያት ቦርዱ እንዲፈርስ መወሰኑን አስታውቋል፡፡



ሀኪንዴ ሂቺለማ

## የደቡብ ኮሪያ ቀዳማዊ እመቤት ምርመራ እየተካሄደባቸው መሆኑ ተገለጸ

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

ቀዳማዊ እመቤት ኪም ኪዮን ሂ በስቶክ ማጭበርበር እና 2,200 ዶላር ዋጋ ባለው የቅንጦት ቦርሳ ጉዳይ በሙስና ተጠርጥረው ምርመራ እየተደረገባቸው መሆኑን ዓቃቤ ሕግ አስታውቋል።

የደቡብ ኮሪያ ቀዳማዊ እመቤት በማጭበርበር ተጠርጥረው እየተመረመሩ መሆኑ ተገለጸ። ይህ ምርመራ እየተካሄደ ያለው ተቃዋሚዎች የመንግሥት የሥነ ምግባር መመሪያ በመጣስ ቅንጡ የዳዮር ቦርሳ የተቀበሉት እና በስቶክ ማጭበርበር ውስጥ ሚና እንዳላቸው በሚጠረጠሩት ቀዳማዊት እመቤት ላይ ልዩ ምርመራ እንዲደረግ ጥሪ እያደረጉ ባለበት ወቅት ነው።

የሴዑል ማዕከላዊ ግዛት የዓቃቤ ሕግ ቢሮ ባወጣው መግለጫ ዓቃቤ ሕግ ባለፈው ቅዳሜ በኪም ላይ "የፊት ለፊት ጥያቄ" ማድረጉን ገልጿል። ባለፈው ዓመት በድብቅ ካሜራ የተቀረጸ ቪዲዮ ኪም 2,200 ዶላር ዋጋ ያለው ቅንጡ ቦርሳ ሲቀበሉ ታይተዋል። የሀገሪቱ ጋዜጦች ይህን ክስተት 'የዳዮር ባግ ስካንዳል' ወይም የዳዮር ቦርሳ ቅሌት ሲሉ ጠርተውት ነበር።

ቅሌቱ ፕሬዚዳንት ዩን ሱክ ዮኦል ፓርቲያቸው ባለፈው ሚያዝያ ወር በተካሄደው ምርጫ እንዲሸነፍ አሉታዊ ተፅዕኖ አድርጓል። ይህ ቀዳማዊ እመቤቷ የተቀበሉት ስጦታ፣ ማንኛውም የደቡብ ኮሪያ መንግሥት ባለሥልጣናት እና ሚስቶቻቸው ከ750 በላይ ዶላር ዋጋ ያላቸውን ስጦታዎች እንዳይቀበሉ የሚከለክለውን ሕግ የሚጥስ መሆኑ ተመላክቷል።

የኪም ረዳቶች ለመርማሪዎች እንደተናገሩት ቀዳማዊ እመቤቷ ቦርሳውን በገዙበት ቀን እንዲመልሱ ቢነገራቸውም፣ ረስተው አለመመለሳቸውን ሮይተርስ ዮንሀፕ ዜና አገልግሎትን ጠቅሶ ዘግቧል።

ዩን የቦርሳውን ቅሌት በተመለከተ በየካቲት ወር ባደረጉት የመጀመሪያ ንግግር ጉዳዩ ፖለቲካዊ ወጥመድ ነው ሲሉ አጣጥለውት ነበር። ዩን እንዳሉት ባለቤታቸው ኪም ስጦታውን የተቀበሉት አልቀበልም ለማለት አስቸጋሪ ስለሆነባቸው ነው ነበር ያሉት። ነገርግን ዩን ዘግየት ብለው በግንቦት በሰጡት መግለጫ የባለቤታቸው ስጦታ መቀበል ተገቢ አለመሆኑን በመግለጽ ይቅርታ ጠይቀዋል።



የፕሬዚዳንት ዩን ሱክ ዮኦል ባለቤት በሙስና ወንጀል ተጠርጥረዋል

# ስፖርት





## 4ኛው ኬሮድ የጎዳና ላይ የሩጫ ውድድር በወልቂጤ

**ቦጋለ አበበ**

ከቅርብ ዓመታት ወዲህ በኢትዮጵያ የተለያዩ ከተሞች የጎዳና ላይ የሩጫ ውድድሮች እየተበራከቱ መጥተዋል። አብዛኞቹ ውድድሮች ትልቅ ዓላማ ሰንቀው ቢጀመሩም ተከታታይነት ሲኖራቸው ግን አይታይም። ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ ካስቆጠረው ታላቁ ሩጫ በኢትዮጵያ በስተቀር ብዙዎቹ የጎዳና ላይ ውድድሮች የአንድ ሰሞን ክስተቶች ብቻ ናቸው።

ስያሜውን በጉራጊኛ ቋንቋ "ኬሮድ" ወይም ሠላም በሚል ያገኘውና በየዓመቱ በወልቂጤና በተለያዩ የጉራጌ ዞን ከተሞች እየተካሄደ የሚገኘው የ15 ኪሎ ሜትር የጎዳና ላይ የሩጫ ውድድር ከተጀመረ አንስቶ ሳይቆራረጥ በየዓመቱ መካሄዱን ቀጥሏል።

ኬሮድ የጎዳና ላይ የሩጫ ውድድር ዘንድሮ ለ4ኛ ጊዜ የ15 ኪሎ ሜትር ውድድሩን ከትናንት በስቲያ በወልቂጤ ከተማ አካሂዷል። የውድድሩን ጥራት ከማሳደግ አንስቶ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተሻሻለ የመጣው የኬሮድ ውድድር ዘንድሮ የተሳታፊዎቹን ቁጥርና የሽልማት ገንዘቡን ከፍ አድርጎ ተካሂዷል። በዚህም መነሻውን ወልቂጤ ከተማ ባደረገው የ15 ኪሎ ሜትር ውድድር ከ21 ክለቦች የተውጣጡ ከስድስት መቶ በላይ ኢሊት አትሌቶች ተሳትፈዋል። አምስት ኪሎ ሜትር በሸፈነው የሕዝብ ሩጫም ከአስራ ስድስት ሺ በላይ ተሳታፊዎች ተካፍለዋል። የአንድ ኪሎ ሜትር የዊልቼር ውድድርም የሩጫው አካል ነበር።



በውድድሩ ከ16ሺ በላይ ሕዝብ በአምስት ኪሎ ሜትር ተሳትፏል፣

ብርቱ ፉክክር ባስተናገደውና በወንዶች መካከል በተካሄደው ውድድር የ3ኛውና የአምናው አሸናፊ አትሌት ጨምዴሳ ደበላ በግል ዳግም የዘንድሮው ውድድር ባለድል ሆኗል። እሱን ተከትሎ የአካባቢው ክለብ ዘቢዳር ያፈራው አትሌት ዘነበ አየለ ሁለተኛ በመሆን ውድድሩን ፈፅሟል። ሌላኛው የግል ተወዳዳሪ ጂግሳ ታደሰ ሦስተኛ ሆኖ ያጠናቀቀ አትሌት ነው።

በሴቶች መካከል በተካሄደውና ተመሳሳይ ርቀት በሸፈነው ውድድር መብሪት ግደይ ከኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ቀዳሚ ሆና ስታጠናቅቅ፣ መቅደስ ሽመልስ በግል ሁለተኛ ሆና ፈፅማለች። ጉተን ሻንቆ ከኦሮሚያ ፖሊስ ሦስተኛ ደረጃን ይዛ ያጠናቀቀች አትሌት ሆናለች።

በውድድሩ ቀዳሚ ሆነው ያጠናቀቁ አትሌቶች እያንዳንዳቸው የአንድ መቶ ሺ ብር ሽልማት ሲያገኙ፣ ሁለተኛ ሆነው የፈፀሙ የ50 ሺ ብር፣ ሦስተኛ ደረጃን የያዙ ደግሞ የ25 ሺ ብር ሽልማት ተረክበዋል። እስከ ስድስተኛ ደረጃ ባለው ያጠናቀቁ አትሌቶችም እንደየደረጃቸው እስከ አምስት ሺ ብር ተሸላሚ ሆነዋል። አምና ቀዳሚ ሆኖ ያጠናቀቀ አትሌት የሚያገኘው የ75 ሺ ብር ሽልማት ዘንድሮ ወደ 100 ሺ ብር እንዳደገም ተጠቁሟል።

የጉራጌ ዞን የውድድሩን መሥራች የቀድሞው አትሌትና የአሁኑ አሠልጣኝ ተሰማ አብሽሮን ጨምሮ ወንድሙ አየለ አብሽሮ፣ የኦሊምፒክ የ10ሺ ሜትር ሻምፒዮኑ ሰለሞን ባረጋ፣ ጥላሁን ኃይሌ፣ አንዱአምላክ በልሁና ሌሎችን ትልልቅ አትሌቶች አፍርቷል። የኬሮድ ውድድርም በአካባቢው ሌሎች ወጣት አትሌቶች ወደ ታላላቅ ውድድሮች የሚሸጋገሩበትና ራሳቸውን የሚያሳዩበት ዕድል በመፍጠር ረገድ ትልቅ አስተዋፅዖ እያበረከተ ይገኛል።

ባለፉት ዓመታትም በዚሁ ውድድር ራሳቸውን አሳይተው በትልልቅ ዓለም አቀፍ የግል ውድድሮችና ሀገራቸውን መወከል የቻሉ በርካታ አትሌቶች ተገኝተውበታል።

በቀጣይ በአጎራባች ዞኖች እንዲሁም በመላው ኢትዮጵያ የውድድሩን አድማስ በማስፋት በየአካባቢው ለሚገኙ ወጣት አትሌቶች ተመሳሳይ የውድድር ዕድል ለመፍጠር ጥረት እየተደረገ እንደሚገኝ የውድድሩ መሥራች አየለ አብሽሮ በጋዜጣዊ መግለጫ ላይ ተናግሯል።

"ለኢትዮጵያ ሠላም እንሩጥ"! በሚል መሪ ቃል የተካሄደው ውድድር ዞኑ በልማቱና በስፖርቱ ዘርፍ ማኅበረሰቡ ተጠቃሚ ለማድረግ የተመሠረተ ነው። በዚህም የሩጫ ውድድሩ ወቅታዊ ችግሮችን በመቅረፉ አንድነትን ለማጠናከር ትልቅ አስተዋፅዖ የሚያበረክት መሆኑን የወልቂጤ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ አቶ እንዳለ ስጦታው ጠቁመው፣ "ውድድሩ ባሕላችንን አጉልተን ያሳየንበት፣ የመቻቻል፣ የመከባበርና የአብሮነት ተምሳሌት የሆነችው ከተማችን ገፅታዋ እንዳይበላሽ ሁሉም በከተማው የሚኖረው ሕዝብ ይህንን ጠብቆ ማቆየት ይኖርበታል።" በማለት ተናግረዋል።

የጉራጌ ዞን ምክትል አስተዳዳሪ አቶ አበራ ወንድሙ በበኩላቸው፣ የዞኑ ማኅበረሰብ በስፖርት ልማት ተሳትፎና ተጠቃሚነት የተገኙ ማኅበራዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳዎችን ከፍተኛ መሆኑን በመረዳት ለስፖርት ልማት ሥራ ልዩ ትኩረት በመስጠት እየሠራ መሆኑን ተናግረዋል። ኢትዮጵያ በምትታወቅበት በአትሌቲክስ ዘርፍ እየተመዘገበ ያለው ውጤት እና እያስገኘ ያለው ጠቀሜታ የበለጠ ጎልቶ እንዲወጣ በማድረግ ስፖርት ለሠላም፣ ለፍቅር እና ለአንድነት በጋራ ቆመን በአትሌቲክስ ዘርፍ ብቁ አትሌቶችን በማፍራት በዓለም አደባባይ ደምቀንና ጎልተን እንድንወጣ ሁላችንም በቅንጅት መሥራት ይጠበቅብናልም ብለዋል።

**ከኢፌዴሪ የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ የሚታተም**

የሴቶችና ማሕበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር
Ministry of Women and Social Affairs

## ያለ ዕድሜ ጋብቻንና የሴት ልጅ ግርዛትን የመከላከል ውጤት

**ሠሳማዊት ውቤ**

ኢትዮጵያ በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችን፤ ያለዕድሜ ጋብቻን፤ ግርዛትንና ሌሎች ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለማስቆም እንደ ሀገር ስትራቴጂ ነድፋ እየሠራች ትገኛለች:: ለአብነትም ባለፉት አሥር ዓመታት ውስጥ ባደረገችው ያላሰለሰ ጥረት የሴት ልጅ ግርዛት በመቀነስ አስደናቂ ውጤት ማስመዝገቧን የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትሯ ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶ/ር) ይናገራሉ::

በቅርቡ በኒውዮርክ ያለ ዕድሜ ጋብቻና የሴት ልጅ ግርዛትን ለማቆምና ለመከላከል ለቻሉ ሀገራት የዕውቅና ሽልማት መርሐ ግብር ተዘጋጅቶ ነበር:: ኢትዮጵያም ያለ ዕድሜ ጋብቻና የሴት ልጅ ግርዛትን የመከላከል ውጤታማ ሥራን መሥራት ከቻሉ ሀገራት መካከል አንዷ ሆናለች:: ኤርጎጌም(ዶ/ር)፣ በተባበሩት መንግሥታት ዋና መሥሪያ ቤት ተገኝተው ሽልማቱን ተቀብለዋል::

በወቅቱ ያለ ዕድሜ ጋብቻና ግርዛትን ለማስወገድ የተቋቋመውን ጥምረት ወክለው ባደረጉት ንግግር ዓለም አቀፉ እውቅናና ሽልማት መንግሥት ለሥርዓተ ፆታ እኩልነትና ሴቶችን ለማብቃት ያለውን ቁርጠኝነት የበለጠ አጠናክሮ እንዲያስቀጥል ስለማስቻሉ አስረድተዋል::

እንደ ሚኒስትራ ገለፃ፣ ለአብነት ኢትዮጵያ ግርዛትን በ2005 ከነበረበት ከ 79 ነጥብ 9 በመቶ ወደ 65 ነጥብ 2 በመቶ መቀነስ ችላለች:: ለዚህም ውጤትም በተለይ ሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶችና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለማስወገድ የሚያግዙ በርካታ የሕግ፣ የፖሊሲና የፕሮግራም እርምጃዎች መወሰዳቸው እንዲሁም ሰፊ ንቅናቄና የግንዛቤ ማስጨበጫ ዘመቻ መካሄዱ ለውጤቱ መገኘት ዐቢይ ምክንያቶች መሆናቸውን አንስተዋል:: ይሁንና ሃገሪቱ የ25 ሚሊዮን የተገረዙ ሴቶችና ልጃገረዶች መኖሪያ እንደመሆኗ አሁንም ግርዛትን ለማስቆም ብዙ ትጋትና ድጋፍ እንደሚጠይቅ አፅዕኖት ሰጥተውታል::

ግርዛትና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊት በልጃገረዶችና በሴቶች ደኅንነት ላይ አካላዊና ሥነ-ልቦናዊ ተፅዕኖ የሚያሳድር ስለመሆኑ የጠቆሙት ሚኒስትሯ፣ በተለይ ግርዛት ከባድ የደም መፍሰስ ያስከትላል፣ ኢንፌክሽን ያመጣል:: በወር አበባ ወቅት ከፍተኛ ሕመምን ማስተናገድ፣ ለራስ የሚሰጥ ግምት ጥሩ አለመሆን፣ የሽንት ቧንቧ ቁስለት፣ መካንነት፣ በወሊድ ጊዜም ችግሮችን ስለማስከተሉ አብራርተዋል::

ከችግሩ አሳሳቢነት አንፃር በአሁን ወቅትም መንግሥት ለጉዳዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራበት እንደሚገኝ አብራርተዋል:: ጉዳዩም የአጀንዳ 2063 እና የ2030 የዘላቂ ልማት አካል ስለመሆኑም ጠቅሰዋል::

ኢትዮጵያ እ.ኤ.አ በ2014 ለንደን ላይ በተካሄደው ዓለም አቀፍ የታዳጊ ሴቶች ጉባዔ ላይ በ2025 የሴት ልጅ ግርዛትንና ያለዕድሜ ጋብቻን ለማስቆም ቃል መግባቷን ያስታወሱት ኤርጎጌ (ዶ/ር)፣ ቃሏን ለማስፈፀም የሕፃናት ጋብቻና የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስቆም የወጣ ብሔራዊ ፍኖተ ካርታ በጉዳዩ ላይ ከሚሠሩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ያልሆኑ አካላት ጋር በመተባበር ስለማዘጋጀቷም ጠቅሰዋል:: ‹‹ፍኖተ ካርታው ለክልሎች ቀርቦ የዕቅዳቸው አካል አድርገው በጀት መድበው እንዲሠሩበትም አቅጣጫ ተቀምጧል›› ብለዋል። ባለድርሻ ዘርፎችም ችግሩን ለመከላከልና ምላሽ ለመስጠት የሚያስችል የማካተት ማዕቀፍ ስለማዘጋጀታቸው አውስተዋል::



**የሴቶችና ማኅበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር**
**ኤርጎጌ ተስፋዬ(ዶ/ር)**

ሚኒስትሯ በመርሐ ግብሩ ኢትዮጵያ ያለ ዕድሜ ጋብቻና የሴት ልጅ ግርዛት ለመከላከል በሠራችው ሥራ የእውቅና ሽልማት ማግኘቷ የበለጠ በጉዳዩ ላይ ተግታ እንድትሠራ የሚያነሳሳት ስለመሆኑም ተናግረዋል::

ውጤቱ እንደሃገር መንግሥት በወሰደው ጠንካራ እርምጃ የተገኘ ስለመሆኑም ጠቁመው፣ በየደረጃው በተደረገ ከፍተኛ ጥረት እንዲሁም በተሠራ ሰፋፊ የግንዛቤና የንቅናቄ ሥራ የተገኘና የሁሉም አካላት ርብርብ ድምር ውጤት ስለመሆኑም አብራርተዋል::

‹‹በቀጣይ በሴቶችና ሕጻናት ላይ የሚደርሱ አካላዊ፣ አእምሯዊ፣ ሥነልቦናዊና ሌሎች ጉዳት የሚያስከትሉ ጥቃቶችንና ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመከላከልና ለማስወገድ ትኩረት ሰጥተን በቅንጅት እንሠራለን›› ብለዋል:: ሥራው በሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ ብቻ ሳይሆን የሁሉንም ርብርብ የሚጠይቅ በመሆኑ ሁሉም የድርሻውን እንዲወጣ ጥሪያቸውን ማቅረባቸውን ከሚኒስቴር መሥሪያ ቤቱ የሕዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ሥራ አስፈፃሚ የተገኘው መረጃ ያመለክታል::

በሴቶች ላይ የሚደርሱ ጥቃቶች ጥቃት በሚል በጥቅሉ ይገለፃሉ:: ይሁን እንጂ ግርዛት፤ ያለ ዕድሜ ጋብቻ፤ ተገድዶ መደፈር፤ ድብደባ፤ ስድብ፤ ዝቅ ተደርጎ መታየት፤ ከወንዶች እኩል እንደማይሠሩና መብት እንደሌላቸው አድርጎ ማሰብ፤ ለከፋ ና ሌሎች በሴቶች ላይ የሚፈፀሙ በደሎችና የኃይል እርምጃዎች በሙሉ ከጥቃት ይመደባሉ::

ጥቃቶቹ በሴቶች ላይ ከሚያሳድሩት አካላዊና ሥነ ልቦናዊ ተፅዕኖ ባሻገር ሌሎች ጫናዎችን እንደሚያሳድሩ የተለያዩ ጥናቶች ይጠቁማሉ:: እንደ ጥናቶቹ በሴቶችን ማኅበራዊ፤ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ተሳትፎና ተጠቃሚነት ላይም ጉልህ ጫና ስለማድረጋቸውም ያትታሉ:: ግርዛትም ሆነ ሌሎቹ ድርጊቶች የሰብዓዊ መብት ጥሰትና ወንጀል ስለመሆናቸውም ያመለክታሉ:: ያለ ዕድሜ ጋብቻና የሴት ልጅ ግርዛትን ለማስወገድ የተቋቋመው ጥምረት እ.ኤ.አ በ2012 ዓ.ም የተመሠረተውም ይሄንኑ ታሳቢ አድርጎ ነው።

በአጠቃላይ እውቅና ሽልማቱ ሀገራት በጉዳዩ ዙሪያ ጠንክረው እንዲሠሩ ያነሳሳል ተብሎ ይታሰባል:: ጅማሮውም ይሄንኑ ታሳቢ ያደረገ ሲሆን የተባበሩት መንግሥታት ሥነ ሕዝብ ሽልማት እ.ኤ.አ በ1981 በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት ጠቅላላ ጉባዔ ነው ለመመስረት የበቃው:: ሽልማቱ በየዓመቱ በሥነ ሕዝብና ሕነ ተዋልዶ ጤና ዙሪያ ልዩ አስተዋፅዖ ላደረጉ ግለሰቦችና ተቋማት ይሰጣል:: ኢትዮጵያም በጉዳዩ ላይ በሠራችው ጠንካራ ሥራ የእውቅና ሽልማቱ ተቋዳሽ ለመሆን በቅታለች::